
# ተልዕኮአችን

መስከረም 2013 | ቅጽ 6



በዚህኛው ቅጽ በወንጌል ስላልተደረሱ የህዝብ
ክፍሎች፣ ስለ አምስቱ የሐይማኖት ክፍሎች እና ስለ አስቸጋሪው የዓለም
ክፍል 10/40 መስኮት በሰፊው የሚዳስ ይሆናል

# መልዕክት

ተልዕኮአችን ዲጅታል መጽሔይት ስድስተኛ ቅጽ በዓማችን ያሉ አምስቱን ያልተደረሱ የሐይማኖት ክፍሎችን ማዕከል አድርጎ ለአንባቢ በቅቷል። በዚህኛው ቅጽ በስፋት ይህንን ለመዳሰስ የታሰበበት ምክኒያት ዛሬ አለማችን በወንጌል ከመደረስ አንጻር ያውን አጠቃላይ መልክ ለአማኙ ማህበረሰብ ከማሳየት አንጻር ነው። ስለሆነም አማኞች በወንጌል ላልተደረሱ ህዝቦች እና የሐይማኖት ክፍሎች ግንዛቤ በማግኘት በወንጌል ተልዕኮ ውስጥ በጸሎት እና በሌሎች መንገዶች ይካፈሉ ዘንድ መልዕክትን እና መጠነኛ የሆነ መረጃዎችን አካተን እነሆ ብለናል።

በዚህ ቅጽ ሌላው በስፋት ለማየት የሞከርነው የዓለማችን አብዛኛው ያተደረሱ የህዝብ ክፍሎች የሚገኙበትን የ10/40 መስኮት ሲሆን ይህን ጽሑፍ ስታነቡ በብዙ እንደምትደነቁና ሌላ ምልከታንም እንደምታገኙበት እምነቴ ነው። መልካም
ንባብ እየተመኘው መጽሔይቱን የምታገኙባቸውን ቻናሎች እንደሚከተለው እገልጻለው ።


መጽሔይቱን የምታገኙባቸው ቻናሎች
Mission talk with Aman (https://t.me/NationsforGod)
Naoel's Perspective (https://t.me/NaolsP)
የቤሪያ ሰዎች በኢትዮጵያ (https://t.me/yeberiyasewoch)
መንፈሳዊ መጽሐፍት (https://t.me/amharicspritualbooks)

በተጨማሪም ጥያቄ እና አስተያየት ካልዎት
በስልክ ቁጥር :- +251920293652/ +251940094767 ይደውሉ
ኢ-ሜይል :- tsionamanuel9@gmail.com ያግኙን

አማኑኤል ገዛኸኝ

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| ለተዘጋጀው ዓለም፤ የተዘጋጀነው እኛ ? | 1 |
| በወንጌል ያልተደረሰው ዓለም፡ 10/40 መስኮት | 2 |
| ያልተደረሱ ቡዲስቶች | 6 |
| ዶ/ር ዶን ሪቻርድሰን ከሰኔ 23, 1935 - ህዳር 23, 2018 የእርቅ ህጻን | 8 |
| ህይማኖት የለሽ ህዝቦች | 10 |
| ህይማኖት የለሽ ህዝቦች ክፍል 1 | 14 |
| የጎሳ እምነት | 16 |
| እስልምና | 17 |
| የሒንዱ እምነት | 18 |
| የአርሲ ኦሮሞ በኢትዮጵያ | 20 |


mi.org

# ለተዘጋጀው ዓለም፤ የተዘጋጀነው እኛ ?

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 28፡ ከ18 – 20 ያለው ወደ ዓለም ሁሉ ሒዱ የሚለለው ትዕዛዝ ለአማኞች ብሎም ለቤተክርስቲያን የተሰጠ ነው። ሆኖም ይህን ትዕዛዝ ከተቀበልን ከ2013 ዓመታት በኃላ እንኳ ያልሄድንባቸው የዓለም ክፍሎች መኖራቸውን ሳስብ ይህ ወንጌልን ለህቦች ሁሉ የማድረስ ተልዕኮ ቅብብሎሽ የትኛው ዘመን ላይ ፍጥነቱ እንደቀነሰ፣ ወንጌልን ያልደረሰበት ቦታ የማድረስ የነጳውሎስ ጥማት እና ረሃብ እንደተገታ ለማሰብ ወደ ኃላ ያስጉዘኛል።

ዛሬ ላይ አለማችን 7.7 ቢሊዮን ሰሆኑ አጠቃላይ ነዋሪዎቿ ተሞልታ እናገኛታላን። ይሁንና ከዚህ ህዝብ 3.23 ቢሊዮን ህዝብ ለአንድ ግዜ እንኳ ክርስቶስ የሚለውን ስም ለመስማት እድል ሳያገኝ ከእግዚአብሔር ፍርድ ዙፋን የማይቀረውን ፍርድ ለመቀበል ቀኑን ይጠብቃል። በዚው መሃል አንድ ሙግት ላንሳ በህይወቶ በእስካሁን ቆይታ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ሲሰበክ የሰሙባቸው ምን ያህል አጋጣሚዎች አሉ? በመቶዎች? በሺዎች ? ወይስ ለአንድ እና ሁለት ግዜያት ? ከዚህ በኃላ የሚሰሙት የወንጌል መልዕክት ፣ መዳን በሌላ በማንም የለም የሚለው የአደባባይ መልዕክት ለእርሶ መዳን እና በእርሶ መዳን ላይ ምን የሚጨምረው አለ ! እርሶ አንዴ ይህን መልዕክት ሰምተው ድነዋላ ዘላለሞን ቀይረዋልና። ታዲያ እርሶ ለአንዴም ይሁን ለሺዎች ግዜያት የሰሙት ወንጌል ሰለ ክርስቶስ ሰምቶ ለማያውቅ ሰው ያለው ትርጉም ምን ሚሆን ይመስላችኃል!!

በዓማችን 17, 441 የህዝብ ክፍሎች አሉ የተለያዩ የቋንቋ ዘዬዎችን (Dialects) ሲጨምር ወደ 24,000 የሚጠጉ የህዝብ ክፍሎች እንዳሉ ይታመናሉ ከእነዚህ ውስጥ 7,407 የሚሆኑት የህዝብ ክፍሎች በወንጌል ያልተደረሱ የምንላቸው ናቸው። እነዚህ በወንጌል ያልተደረሱ ህዝቦች በአምስት ዋና ዋና የሀይማኖት ክፍሎች የሚመደቡ ሆነው እናገኛቸዋለን። እነርሱም እስልምና ፣ ቡዲዝም፣ ሒንዱይዝም፣ የጎሳ ሐይማኖት እና ሐይማኖት የለሽ ናቸው።

ዛሬ ላይ እነዚህ ህዝቦች የት እና በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ የሚታወቅ፤ ስለ እነርሱ በቂ የሚባሉ መረጃዎች ለአማኙ ማህበረሰብ እና ለቤተክርስቲያን ያሉ ቢሆንም በአማኙ ማህበረሰብ ያለው እንቅስቃሴ እና የተፈጠሩ ንቅናቄዎችን ለመደገፍ የሚደረገው ጥረት ዝቅተኛ መሆን እነዚህ የህዝብ ክፍሎች የሚደረሱበተ ዘመን ገና ሩቅ እንደሆነ እንድናስብ የሚያደርግ ነው። በርግጥ ያልተደረሱ የሚባሉት የህዝብ ክፍሎች ያልተደረሱት መደረስ ስለማይችሉ ሳይሆን ልንደርሳቸው የተገባን እኛ ሐላፊነታችንን እየተወጣን ስላልሆነ ብቻ ነው።

## <u>ታዲያ ምን እናድርግ የብዙ አማኞች ጥያቄ ነው?</u>

ይህን ከመረዳት እንጀምር ! በእግዚአብሔር ተልዕኮ ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ ሰራተኛ መሆን እጅግ ታላቅ እድል ነው። ወደ አለም ሁሉ ሒዱ የሚለው የሆነ የፓስተር፣ ወንጌላዊ፣ ነብይ፣ ሐዋርያ ትዕዛዝ ሳይሆን የራሱ የክርስቶስ ነው። ታዲያ እሺ ስንል ስንታዘዝ የታዘዝነው ለጌታችን እና መድሃኒታችን የክርስቶስ ትዕዛዝን ነው።

ቀጥሎም ይህን ለመረዳት ግዜ እንውሰድ ! በተልዕኮ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ ሰራተኛ መሆን ስንል ሚሲዮናዊ መሄድ ብቻ እያልን አለመሆኑን። ወንጌል ወዳልደረሳቸው ህዝቦች መሄድ በተልእኮው ሜዳ ከእርሱጋር ተሳታፊ መሆን የምንችልባቸው መንገዶች መሃል አንዱ እንጂ ብቸኛው አይደለም ታዲያ ጸሎታችን ህዝቦች በወንጌል ይደረሱ ዘንድ እና ለሚሄዱ ሚሲዮናውያን ሲሆን፣ ወደ አካባቢያችን ወንጌል ካልደረሳቸው ህዝቦች ሚመጡ ሰዎችን ወዳጅ በማድረግ ወንጌል የሚሰሙበት እድል ስንሆን፣ ሌሎች አማኞች ለወንጌል ልብ እና ሸክም ይኖራቸው ዘንድ የማነቃቃት ስራ ስንሰራ እና በገንዘባችን ወንጌል እንዲሰራ ከምናገኘው ላይ የወንጌል ደጋፊ ከሆንን በዚህ ወደ ዓለም ሁሉ ሒዱ በሚለው ትዕዛዝ ውስጥ ተሳታፊዎች ነን እግዚአብሔርም ሚፈልገው ይህን ነውና ደስታው ሙሉ ነው።
ጌታሆይ ጸሎቴ ይህ ነው። በምቾት ክልላችን ተደላድለን ከአንተ ጋር አብሮ ለመስራት ያገኘነውን ይህን አስደናቂ እድል እንዳናባክን፣ በቸልተኛነታችን እንዳንሸነፍ እለምንሃለው። አንተ ህዝቦች ሁሉ ይድኑ ዘንድ ያለህን ያንን ናፍቆት መካፈል ይሁንልን።
ቀድሞ ወንዝ በወረደበት ቦታ ሁሉ ወንጌልህ እንደገና ይፍሰስ !! ሉተር ዊሻርድ
አማኑኤል ገዛኸኝ
የተልዕኮ አስተማባሪ !!

# በወንጌል ያልተደረሰው ዓለም፡ 10/40 መስኮት

የ 10/40 መስኮት የሰሜን አፍሪካን፣ የመካከለኛው ምስራቅ እና እስያን የሚያካትት በአስር ዲግሪ ሰሜን እና 40 ዲግሪ ሰሜን ኬንትሮስ(ላቲቲዩድ) የሚገኝ የአራት መዐዘን ቅርጽ ያለው ክልል (ቦታ) ነው። 10/40 መስኮት ብዙውን ጊዜ"ተከላካይ ቀበቶ" ወይም"ሬዚስታንስ ቤልት" ተብሎ የሚጠራ ሲሆን አብዛኞቹን የዓለም ሙስሊሞች፣ ሂንዱዎች እና ቡድሂስቶችንም አጠቃሎ የያዘ ክልል ነው።
የመጀመሪያው 10/40 መስኮት ቢያንስ 50 ፐርሰንት የሚሆነው የቆዳ ስፋታቸው በ 10 እና 40 ዲግሪ ሰሜን ኬንትሮስ (ላቲቲዩድ) ውስጥ የሚገቡ ሀገራትን ብቻ የሚያካትት ነበር። የተሻሻለው 10/40 መስኮት ለ 10 ወይም 40 ዲግሪ ሰሜን ኬንትሮስ (ላቲቲዩድ) ቅርብ የሆኑና እና ከፍተኛ በወንጌል ያልተደረሰ ህዝብ መጠን ያላቸውን ብዙ ተጨማሪ ሀገሮችን አካቷል። የመጀመሪያውን እና የተሸሻለውን ሀገራት ዝርዝር በዚሁ ጽሑፍ ላይ አካተንላችኃል ይመልከቱት።

በ 8946 የተለያዩ ህዝብ ክፍሎች ውስጥ የሚኖሩ ወደ 5.16 የሚጠጉ ግለሰቦች በተሻሻለው የ10/40 መስኮት ክልል ውስጥ ተካተዋል። ከእነዚህ ሰዎች መካከል 6205 (69.4%) በወንጌል ያልተደረሱ ተብለው ሚታሰቡ እና 3.12 ቢሊዮን ያህል ህዝብ ቁጥር አላቸው። ይህ ማለት በ10/40 መስኮት ውስጥ ካሉት ግለሰቦች መካከል በግምት 61% የሚሆኑት ባልተደረሱ የህዝብ ክፍል ውስጥ ይኖራሉ ማለት ነው። የ10/40 መስኮት በዓለም ላይ በከፍተኛ ሁኔታ በወንጌል ያልተደረሱ የህዝብ ክፍሎች መገኛ የሆኑ እንደ ሻኢክ፣ ያዳቫ፣ ቱርኮች/ቱርክ፣ የሞሮኮ አረቦች፣ ፓሽቱን፣ ጃት፣ እና በርሜስ ያሉ ህዝቦች መገኛ ነው።

Ø የ 10/40 መስኮት በዓለም ላይ ከፍተኛ በወንጌል ያልተደረሱ ህዝብ ክፍሎች መገኛ ነው።
የ10/40 መስኮት በርካታ አስፈላጊ የምንላቸው ምልከታዎች አሉት፦

1. ታሪካዊ እና መፅሀፍ ቅዱሳዊ ጠቀሜታው
2. ወንጌል ያልደረሳቸው ሀገራት
3. ያልተደረሱ የህዝብ ክፍሎች እና ከተሞች
4. የሶስት ሀይማኖታዊ ቡድኖች የበላይነት
5. የድሆች(ቅድመ) ሁኔታ
6. በ10/40 መስኮት ውስጥ ያሉ ከፍተኛ የሰይጣን ምሽጎች።

## የ10/40 መስኮት ታሪካዊ እና መፅሀፍ ቅዱሳዊ ምልከታዎቹ

የእየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች በ10/40 መስኮት ላይ ማተኮር ያለባቸው የመጀመሪያው እና መሰረታዊው ምክንያት የዚህ አካባቢ መፅሀፍ ቅዱሳዊ እና ታሪካዊ ጠቀሜታ ነው። መፅሀፍ ቅዱስ የሚጀምረው አሁን ባለው የ10/40 መስኮት ላይ ባለው ልብ ውስጥ ያስቀመጣቸውን የአዳምና የሄዋን ዘገባ ነው። የእግዚአብሄር ሀሳብ፤ በዘፍጥረት 1፡26 ላይ እንደገለፀው፤ የሰው ልጆች ምድርን ሙሉ በሙሉ እንዲገዙ ነበር። ሆኖም አዳምና ሄዋን በእግዚአብሄር ላይ በማመጽ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ተላልፈው የመግዛት መብታቸውን አጡ። እግዚአብሔር ምድር ላይ በከባድ ጎርፍ ፍርድን እስኪያደርግ ድረስ የሰው ሀጥያተኝነት እየጨመረ መጣ። በዚህም ሳያበቃ የሰው ልጅ ታላቁን የባቢሎንን ግንብ በመገንባት አዲስ ግዛትን የማቋቋም ከንቱ ሙከራ ሲያደርግ እንመለከታለን። ይህ በ10/40 መስኮት እምብርት ውስጥም የተከናወነው ሙከራ በእግዚአብሄር ላይ ግልፅ ማቃለያ ነበር። በድጋሚም እግዚአብሄር እጁን ለፍርድ አነሳ/ ዘረጋ። ውጤቱም የተለያዩ ቋንቋዎችን ማስተዋወቅ፤ የምድርን ህዝቦች መበታተን እና ብሄሮችን መመስረት ሆነ።

Ø የ10/40 መስኮት የአለም አብዛኛው ወንጌል ያልደረሰበት ሀገሮች መኖሪያ ነው

Ø የ10/40 መስኮት ወንጌል በደንብ ያልደረሰባቸው ሀገራት ስብስብ ነው

የ10/40 መስኮት የአለም አብዛኛው ወንጌል ያልተሰበከባቸው ሀገራት መኖሪያ ነው ።"በወንጌል ያልተደረሱ" የሚባሉት ሰዎች ስለ ወንጌል አነስተኛ እውቀት ያላቸው ግን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ትክክኛ ዕድል የሌላቸው/ ያላገኙ ናቸው። ከአጠቃላይ የምድር የቆዳ ስፋት 1/3ተኛውን ብቻ የሚይዝ ቢሆንም ወደ 2/3ተኛ የሚሆነውን የአለም ህዝብ የሚኖረው በ10/40 መስኮት ውስጥ ነው። የመጀመሪያው የ10/40 መስኮት 50% የሚሆነው የቆዳ ስፋታቸው በሰሜን ኬንትሮስ (ላቲቲዩድ) ውስጥ የሚገኙ ሀገራትን ብቻ የሚያካትት ነበር። የተሻሻለው የ10/40 መስኮት እንደ ደቡብ ኮሪያ እና ፊሊፒንስ ያሉ ክርስቲያናዊ የሆኑ ብዙ ሃገራትን አስወግዶ እንደ ኢንዶኔዢያ ያሉ ወደ 10 ወይም 40 ዲግሪ ሰሜን ኬንትሮስ (ላቲቲዩድ) አቅራቢያ የሚገኙ እና ወንጌልን ያልሰሙ ብዙ ሰዎች ያለባቸውን ሌሎች ብዙ ሀገራትን ያካትታል።

Ø የ10/40 መስኮት በወንጌል ያልተደረሱ ህዝቦች እና ከተሞች

የቀጠለ....

# በወንጌል ያልተደረሰው ዓለም፡ 10/40 መስኮት

የ 10/40 መስኮት የሰሜን አፍሪካን፣ የመካከለኛው ምስራቅ እና እስያን የሚያካትት በአስር ዲግሪ ሰሜን እና 40 ዲግሪ ሰሜን ኬንትሮስ(ላቲቲዩድ) የሚገኝ የአራት መዐዘን ቅርጽ ያለው ክልል (ቦታ) ነው። 10/40 መስኮት ብዙውን ጊዜ"ተከላካይ ቀበቶ" ወይም"ሬዚስታንስ ቤልት" ተብሎ የሚጠራ ሲሆን አብዛኞቹን የዓለም ሙስሊሞች፣ ሂንዱዎች እና ቡድሂስቶችንም አጠቃሎ የያዘ ክልል ነው።

የመጀመሪያው 10/40 መስኮት ቢያንስ 50 ፐርሰንት የሚሆነው የቆዳ ስፋታቸው በ 10 እና 40 ዲግሪ ሰሜን ኬንትሮስ (ላቲቲዩድ) ውስጥ የሚገቡ ሀገራትን ብቻ የሚያካትት ነበር። የተሻሻለው 10/40 መስኮት ለ 10 ወይም 40 ዲግሪ ሰሜን ኬንትሮስ (ላቲቲዩድ) ቅርብ የሆኑና እና ከፍተኛ በወንጌል ያልተደረሰ ህዝብ መጠን ያላቸውን ብዙ ተጨማሪ ሀገሮችን አካቷል። የመጀመሪያውን እና የተሸሻለውን ሀገራት ዝርዝር በዚሁ ጽሑፍ ላይ አካተንላችኃል ይመልከቱት።

በ 8946 የተለያዪ ህዝብ ክፍሎች ውስጥ የሚኖሩ ወደ 5.16 የሚጠጉ ግለሰቦች በተሻሻለው የ10/40 መስኮት ክልል ውስጥ ተካተዋል። ከእነዚህ ሰዎች መካከል 6205 (69.4%) በወንጌል ያልተደረሱ ተብለው ሚታሰቡ እና 3.12 ቢሊዮን ያህል ህዝብ ቁጥር አላቸው። ይህ ማለት በ10/40 መስኮት ውስጥ ካሉት ግለሰቦች መካከል በግምት 61% የሚሆኑት ባልተደረሱ የህዝብ ክፍል ውስጥ ይኖራሉ ማለት ነው። የ10/40 መስኮት በዓለም ላይ በከፍተኛ ሁኔታ በወንጌል ያልተደረሱ የህዝብ ክፍሎች መገኛ የሆኑ እንደ ሻኢክ፣ ያዳቫ፣ ቱርኮች/ቱርክ፣ የሞሮኮ አረቦች፣ ፓሽቱን፣ ጀት፣ እና በርሜስ ያሉ ህዝቦች መገኛ ነው።

Ø የ 10/40 መስኮት በዓለም ላይ ከፍተኛ በወንጌል ያልተደረሱ ህዝብ ክፍሎች መገኛ ነው።

የ10/40 መስኮት በርካታ አስፈላጊ የምንላቸው ምልከታዎች አሉት፡-

1. ታሪካዊ እና መፅሀፍ ቅዱሳዊ ጠቀሜታው
2. ወንጌል ያልደረሳቸው ሀገራት
3. ያልተደረሱ የህዝብ ክፍሎች እና ከተሞች
4. የሶስት ሀይማኖታዊ ቡድኖች የበላይነት
5. የድሆች(ቅድመ) ሁኔታ
6. በ10/40 መስኮት ውስጥ ያሉ ከፍተኛ የሰይጣን ምሽጎች።

## የ10/40 መስኮት ታሪካዊ እና መፅሀፍ ቅዱሳዊ ምልከታዎቹ

የእየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች በ10/40 መስኮት ላይ ማተኮር ያለባቸው የመጀመሪያው እና መሰረታዊው ምክንያት የዚህ አካባቢ መፅሀፍ ቅዱሳዊ እና ታሪካዊ ጠቀሜታ ነው። መፅሀፍ ቅዱስ የሚጀምረው አሁን ባለው የ10/40 መስኮት ላይ ባለው ልብ ውስጥ ያስቀመጣቸውን የአዳምና የሄዋን ዘገባ ነው። የእግዚአብሄር ሀሳብ፤ በዘፍጥረት 1:26 ላይ እንደገለፀው፤ የሰው ልጆች ምድርን ሙሉ በሙሉ እንዲገዙ ነበር። ሆኖም አዳምና ሄዋን በእግዚአብሄር ላይ በማመጽ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ተላልፈው የመግዛት መብታቸውን አጡ። እግዚአብሔር ምድር ላይ በከባድ ጎርፍ ፍርድን እስኪያደርግ ድረስ የሰው ሀጥያተኝነት እየጨመረ መጣ። በዚህም ሳያበቃ የሰው ልጅ ታላቁን የባቢሎንን ግንብ በመገንባት አዲስ ግዛትን የማቋቋም ከንቱ ሙከራ ሲያደርግ እንመለከታለን። ይህ በ10/40 መስኮት እምብርት ውስጥም የተከናወነው ሙከራ በእግዚአብሄር ላይ ግልፅ ማቃለያ ነበር። በድጋሚም እግዚአብሄር እጁን ለፍርድ አነሳ/ ዘረጋ። ውጤቱም የተለያዩ ቋንቋዎችን ማስተዋወቅ፤ የምድርን ህዝቦች መበታተን እና ብሄሮችን መመስረት ሆነ።

Ø የ10/40 መስኮት የአለም አብዛኛው ወንጌል ያልደረሰበት ሀገሮች መኖሪያ ነው

Ø የ10/40 መስኮት ወንጌል በደንብ ያልደረሰባቸው ሀገራት ስብስብ ነው።

የ10/40 መስኮት የአለም አብዛኛው ወንጌል ያልተሰበከባቸው ሀገራት መኖሪያ ነው ።"በወንጌል ያልተደረሱ" የሚባሉት ሰዎች ስለ ወንጌል አነስተኛ እውቀት ያላቸው ግን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ትክክኛ ዕድል የሌላቸው/ ያላገኙ ናቸው። ከአጠቃላይ የምድር የቆዳ ስፋት 1/3ተኛውን ብቻ የሚይዝ ቢሆንም ወደ 2/3ተኛ የሚሆነውን የአለም ህዝብ የሚኖረው በ10/40 መስኮት ውስጥ ነው። የመጀመሪያው የ10/40 መስኮት 50% የሚሆነው የቆዳ ስፋታቸው በሰሜን ኬንትሮስ (ላቲቲዩድ) ውስጥ የሚገኙ ሀገራትን ብቻ የሚያካትት ነበር። የተሻሻለው የ10/40 መስኮት እንደ ደቡብ ኮሪያ እና ፊሊፒንስ ያሉ ክርስቲያናዊ የሆኑ ብዙ ሃገራትን አስወግዶ እንደ ኢንዶኔዢያ ያሉ ወደ 10 ወይም 40 ዲግሪ ሰሜን ኬንትሮስ (ላቲቲዩድ) አቅራቢያ የሚገኙ እና ወንጌልን ያልሰሙ ብዙ ሰዎች ያለባቸውን ሌሎች ብዙ ሀገራትን ያካትታል።

Ø የ10/40 መስኮት በወንጌል ያልተደረሱ ህዝቦች እና ከተሞች

የቀጠለ....

# በወንጌል ያልተደረሰው ዓለም፡ 10/40 መስኮት

6205 በሚደርሱ የህዝብ ክፍሎች ውስጥ ወደ 3.12 ቢሊዮን የሚጠጉ ሰዎች /ግለሰቦች በ10/40 መስኮቱ አብዛኛውን በወንጌል ያልተደረሱ የሚባሉ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የህዝብ ቁጥር ያላቸው ትልልቅ ከተሞችን ይይዛል። የመጀመሪያዎቹ 50 በጥቂቱ የተደረሱ/ ያልተደረሱ የሚባሉት ትላልቅ ከተሞች ሁሉም በዚህ 10/40 መስኮት ውስጥ ይገኛሉ! ይህ እውነት ብቻ በ10/40 መስኮት የሚደረገው ተልዕኮ ስራ/ጥረት ለምን ቅድሚያ መስጠት እንደሚያስፈልግ አጉልቶ ያሳያል።

Ø የ10/40 መስኮት በአለም ላይ ያሉ አራቱን ዋና ዋና ሀይማኖታዊ ቡድኖች ይይዛል።
Ø የ10/40 መስኮት የሶስት ሀይማኖት ቡድኖች የበላይነት የታየበት ነው።

የ10/40 መስኮት በአለም ላይ ያሉ ዋና ዋና የሀይማኖት ቡድኖችን ያካትታል/ይይዛል። አብዛኛው የእስልምና ፣ የሂንዱ እና የቡድሂዝም እምነት ተከታዮች እንዲሁም ሀይማኖት የሌላቸው ሰዎች በ10/40 መስኮት ውስጥ ይኖራሉ። በ10/40 መስኮት በግራ በኩል ወይም በምእራባዊው ክፍል የሙስሊሙ ዓለም ሚባል እና በሰሜን አፍሪካ በኩል እስከ መካከለኛው ምስራቅ ድረስ ባለው ሰፊ ክፍል ውስጥም ጎልቶ የሚታይ ነው። በ10/40 መስኮት መሀከለኛው ክፍል የምትገኘው ደቡብ እስያ የ33 ሚሊዮን አማልክት ያሉት የሂንዲይዝም መገኛ(ልብ) ናት። ይህም የ10/40ውን የቀኝ ክፍል ወይም ምስራቅ ክፍል ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል። ቡድሂዝም በደቡብ ምስራቅ እስያ ውስጥ ዋነኛው ሀይማኖት ነው፤ ምንም እንኳን ከ1940ዎቹ ከማርክሲስት አብዮት ጀምሮ በይፋ አምላክ የለሽ አገር ያደረጋት ቢሆንም ቻይና ግን በቡድሂዝም ከፍተኛ ተፅዕኖ ስር እየኖረች።

## ü የ10/40 መስኮትና ድህነት

10/40 መስኮት ብዙሀኑ የአለም ድሆች መኖሪያ ነው። የድሀ ድሀ ከሚባሉት ከአስሩ ከስምንት በላይ የሚኖሩት በ10/40 መስኮት ውስጥ ነው። በአማካይ በአመት በግለሰብ ደረጃ ከጥቂት መቶ ዶላሮች ባነሰ ገንዘብ ይኖራሉ። ‹‹ ድሆች ጠፍተዋል፣ የጠፉትም ድሆች ናቸው›› እንደሚባለው ብዙሀኑ በወንጌል ያልተደረሱት ህዝቦች የሚኖሩት በዓለም ላይ ባሉ ደሀ ሀገራት ውስጥ ነው። በድሀው የዓለም ሀገራት እና በወንጌል ባልተደረሱ መካከል አስገራሚ ጥምረቶች ይታያሉ።

## ü የ10/40 መስኮትና ጠንካራ መንፈሳዊ ግምባር

የ10/40 መስኮት ብዙ መንፈሳዊ ጠንካራ ግምባሮችን ያካትታል። በ10/40 መስኮት ውስጥ የሚኖሩት በቢሊየኖች የሚቆጠሩ ሰዎች በድህነትና በሽታ ከመጎዳታቸውም ባሻገር ከሚለውጠው የወንጌል ሀይል ርቀዋል። 2 ቆሮንቶስ 4፡4 ላይ የተገለፀው እውነት አሳዛኝ ምሳሌዎች ናቸው። ይኸውም ‹‹ ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው የዚህ ዓለም ገዢ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ›› የሚለው ነው።

## ü የ10/40 መስኮትና የታደሰ ትኩረት

ከ200 አመታት በፊት የክርስቲያን ተልዕኮዎች ትኩረት በዓለም ዙሪያ ባሉት የባህር ዳርቻዎች ለነበሩ ማህበረሰቦች ነበር ። ከአንድ ምዕተ ዓመት በኋላ የባህር ዳርቻዎች ጥረት ስኬት ሌላ አዲስ ትውልድ ወደ አህጉራት ውስጣዊ አካባቢዎች እንዲደርስ አነሳሳው። ባለፉት በርካታ አስርት አመታት ውስጥ በአህጉራቱ ውስጥ ያለውአገልግሎት ስኬት በህዝብ ክፍሎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት እንዲደረግ አስችሏል። ዛሬ የክስቶስ ተከታዮች ጥረታቸውን ወዳልተደረሱ የዓለም ህዝቦች ላይ እያደረጉ ነው። ከእነዚህም አብዛኞቹ በ10/40 መስኮት ያሉ ናቸው።

- ከዓለም የደሀ ደሀ 82% (በነፍስ ወከፍ GNP በዓመት ከ500 የአሜሪካ ዶላር ያነሰ) ያገኛሉ።
- 84% ዝቅተኛ የህይወት ጥራት ያላቸው ( የህይወት ዕድሜ፣ የህፃናት(አራስ) ሞት እና ማንበብና መፃፍ) ሰዎች የሚገኙት እዚህ ስፍራ ላይ ነው።
- ከክርስትና ውጪ የዓለም ዋና ሀይማኖቶች ማዕከል( እስልምና፣ ቡድሂዝም፣ ሂንዱኢዝም ወዘተ) በስፋት የሚገኙበት ስፍራ ነው።

የቀጠለ....

· ወደ 100% የሚጠጉ በጣም ደሀ የሆኑና ክርስቲየኖችን በአቅራቢያቸው ሊያገኙ የማይችሉ ሰዎች ይገኙበታል ( ሁለት ጉንዮስ ትንታኔ) (analysis)

· አነስተኛ የክርስቲያን አቅርቦት፣ ኢንቨስትመንት እና ወንጌል ላማድረስ በጣም አነስተኛ እንቅስቃሴ ሚደረግበት ቦታ ነው። የGIS ትንታኔ በሀገር ደረጃ ያለ መረጃ ከ‹‹ኦፕሬሽን ወርልድ›› ፣ ‹‹ከ H ወርልድ ክስቲያን ኢንሳይክሎፒዲያ›› እና ‹‹ ከወርልድ ፌስቡክ›› ተጠቅሟል።

## ü በ10/40 መስኮት ውስጥ ክርስቲያን ያልሆኑ በሀይማኖት ክፍል ሲታይ

የ GIS ትንታኔ የመጀመሪያ ዕትም በ10/40 መስኮት ያሉ 3 ዋና የሀይማኖት ቡድኖችን አጉልቶ ያሳያል። ለመጥቀስም አብዛኛው ሙስሊም፣ ሂንዱ እና ቢድሂስት የሆኑ ህዝቦች ናቸው። በዛን ጊዜ እ.ኤ.አ በ2000 ዓ.ም (ከኦፕሬሽን ወርልድ) የነበረው የህዝቡ ብዛት ግመት እንደሚከተለው ተነስቷል።

· 28 የሙስሊም ሀገራት 1.1 ቢሊዮን የህዝብ ብዛት ግምት(2000)
· 2 የሂንዱ ሀገራ 1.1 ቢሊዮን የህዝብ ብዛት ግምት (2000)
· 8 የቢድሂስት ሀገራት 237 ሚሊዮን የህዝብ ብዛት ግምት(2000) በኋላ የተደረጉ ማሻሻያዎች የወደፊትን የህዝብ ብዛት ግንዛቤ ውስጥ ካስገባ ግምት ይልቅ የበለጠ የተመሰረቱት የህዝብ ቆጠራ እና ሌላ ግምቶች ላይ ነው። የተጠቀሰው ማጣቀሻ ያልተደረሱ ክስቲያን ያልሆኑ በ10/40 መስኮት ውስጥ ያሉ የህዝብ ብዛት ግምትን እንደሚከተለው ያቀርባል፡-
· 856 ሚሊዮን ሙስሊሞች
· 550 ሚሊዮን ሂንዱዎች
· 275 ሚሊዮን ቢድሂስቶች
· 140 ሚሊዮን በ2550 የህዝብ ክፍሎች( በዋነኝነት አኒሚስቶች)
· 17 ሚሊዮን አይሁዶች

ü በ10/40 መስኮት ያሉ ሀገራት/ ህዝቦች

በመጀመሪያ የ10/40 መስኮት የሚከተሉትን 57 ሀገራት ያካተተ ነበር። በአቅራቢያ ያሉትን አንዳንድ አስፈላጊ ሀገራትን ያካተተ ሰፋ ያለ ዝርዝር በጆሸዋ ፕሮጀክት ቀርቧል።

1. አፍጋኒስታን
2. አልጄሪያ
3. ባህሬን
4. ባንግላዲሽ
5. ቤኒን
6. ቡታን
7. ቡርኪና ፋሶ
8. ካምቦዲያ
9. ቻድ
10. ቻይና
11. ሳይፕረስ
12. ጅቡቲ
13. ግብፅ
14. ኤርትራ
15. ኢትዮጵያ
16. ጋምቢያ
17. ጊኒ
18. ጊኒ-ቢሳው
19. ህንድ
20. ኢራን
21. ኢራቅ
22. እስራኤል(ፍልስጤምን ጨምሮ)
23. ጃፓን
24. ጆርዳን
25. ኮሪያ(ሰሜን)
26. ኮሪያ(ደቡብ)
27. ኩዌት
28. ላኦስ
29. ሌባነን/ሊባኖን
30. ሊበያ
31. ማሊ
32. ማልታ
33. ማውሪታኒያ
34. ሞሮኮ
35. ማይናማር
36. ኔፓል
37. ኒገር
38. ኦማን
39. ፓኪስታን
40. ኳታር
41. ሳውዲአረቢያ
42. ሴኔጋል
43. ሲዳን(በወቅቱ ደቡብ ሱዳንን ጨምሮ)
44. ሲሪያ
45. ታይዋን
46. ታጃኪስታን
47. ታይላንድ
48. ቱኒዚያ
49. ቱርክ
50. ቱርክሜኒስታን
51. የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ
52. ቬትናም
53. ምዕራባዊ ሰሀራ
54. የመን

እነዚህ ሁሉ እ.ኤ.አ ከ1990 አንስቶ ቢያንስ 50 በመቶ የመሬት ስፋታቸውን ከ10-40ድግሪ ኬንትሮስ (ላቲቲዩድ) ውስጥ ያረፈ የብሉይ ዓለም ሀገሮች(old world nations) (በአብዛኛው በምስራቅ ሄሚስፈር ወይምንቅፈ ክበብ) ያሉ ናቸው። (ዝርዝሩ ጂብራልታርንና ማካውን አካትቷል እነዚህ ሀገራት ነጻ (Independent) ሀገራት አይደሉም)።

ትርጉም ፡- ህልዳና ብሩክ
ኮምፒውተር ጽሁፍ ፡- ረድኤት ብርሃኑ እና ህይወቴ ታደሰ
ምንጭ ፡- Wikipedia, Joshua project እና Howard Culbertson



የዓለማችን ያልተደረሱ የሐይማኖት ክፍሎች

# ቡዲዝም

**አጠቃላይ የእምነቱ ተከታዮች**

**- 495,820,000 -**

**አለም አቀፍ የህዝብ ብዛት በ% ሲሰላ**

**- 6.5 % -**

**የሚገኝበት የህዝብ ክፍሎች ብዛት**

**- 667 -**

**ያልተደረሱት የህዝብ ክፍሎች**

**- 524 (78.6 %) -**

# ያልተደረሱ ቡዲስቶች

በቲቤት፣ታይላንድ፣ቬትናም፣ሴሪላንካና በሌሎች ብዙ ቡዲስት ሀገራት ቡርትካናማ የለበሱ መነኮሳት በእያንዳንዱ ጠዋት ቤት ለቤት እየዞሩ ምግብ ይሠበስባሉ። ስለተሠጣቸው ነገር ምስጋናን አያቀርቡም ምክንያቱም ከሞት በኃላ ሌላ ስጋን ለብሶ በመነሳት እምነት የተሻለ ደረጃን እንዲያገኙ ዉለታን እየዋሉላቸው እንደሆነ ስለሚያስቡ።
ቡዲዝም በሲደርታ ጋውሌማ የስድስተኛ መቶ አመት (አመተ አለም) አስተምህሮ ላይ የተመሰረተ ነው። ወደ በኃላ ሲደርታ ቡድሃ በመባል መጠራት ጀመረ።ህይወት የህመም ንድፍና በምኞት ምክንያት የሚመጣ ጭንቅ ውጤት እንደሆነች አስተምሯል ።የሰውን ምኞት መግታት ፣ለጭንቅ ፍፃሜ ምልክት ነው። የህይወት ግብ ምኞትን ወደማስቀረት በፍጥነት መራመድ ነዉ። ይሄም ነርቫና በመባል ይታወቃል።





በሶስተኛ መቶ አመት (አመተ አለም) በአሁን በሴሪላንካ ደሴት ላይ ፣የቡዲስት አስተምህሮ በፖሊ ቋንቋ (ከሳን ስክሪፕት ጋር የተያያዘ ) በፅሁፍ ተጠናቆ ነበር።

ሀይማኖታዊ ያልሆነ ፣ፍልስፍናዊ የቡድሂዝም ጎኖችጎኖች፡-ከአምላክ ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም። ይህ ግልጽ የሆነ ህግ ነው። አስተምሮቱ ነፍስ እንደሌለ ይገልጻል። የማንነት ማህከል የለም። ባይሆን ሰው የ አምስት "ካህንዳዎች ድምር ነው።እነዚህም የማንነት ምስያ ይሰጣሉ። ይህም የማንነት ምስያ ጭንቀት፣ውጥረትና ምኞት በስነስርዓቱ ሲወገዱ ይጠርጋል። ስነስርዓት እየዋለ እያደረ ሀርነርቫና ይወስዳል ።(ባዶነትና ራቁትነት)ምኞትን የማጣት ደረጃ ፍፁም ሰላምንና ፍፁምነትን ያስገኛል።



የቡዲዝም ታዋቂ ልምምድ አብዛኛውን ጊዜ ሽልማት የሚያስገኙ ስራዎችን መስራትና ክብረ በአላትን ድግሶችን ያካትታል ።

የቀጠለ....

በቡድሂስት ሀገራት ዜጎች የመነኮሳት ዜማ "ሲትራ"፣ የተጠበቀ የምርቃት ደንብ፣በቤት ክብረ በዓላት ላይ ከለላ ፣በቀብር እና የመታሰቢያ ስርዓት ላይ ለሟች ጥቅም ሬሳ የማቃጠል ተግባር ያከናውናሉ።



ቡድሂዝም ለተፋላሚው ስምንት እጥፍ ክብር ከአምስት አታድርጉ ጋር ያስቀምጣል እነሱም አትስረቅ፣ አትዋሽ ፣ አታመንዝር ፣አትጠጣ (አትስከር) የሚሉ ናቸው። አብዛኛው የቡድሂዝም እምነት ተከታዮች ግዴታዎቻቸውን ለመቀነስና ሽልማት ለማግኘት ቀላል ንድፍ ይከተላሉ። ካርማ በአንድ ሰው ህይወት ውስጥ የመጥፎና መልካም ተግባሮች ድምር ነው።ቡድሂዝም በብዙሃኑ እንደሚደረገው ሽልማት ለሚያስገኙ መነኮሳት መልካም ተግባርን ማድረግ ፣ በክብረ በዓላትና መንፈሳዊ ስርዓቶች ላይ መሳተፍ ፣ለቡድሂስት
ቤተ መቅደስ እድሳትና ግንባታ መዋጮ ማድረግ መሠረታዊ ነገር ነው።



ምንም እንኳ ቡድሂዝም ሰዎች በሳምሳራ ተይዘው እንዳሉ ቢያስተምርም፣ የሰው ውልደት እና ሞት የዘለአለም ኡደት ፣ላልተወሰነ ጊዜ ቀጣይነት ያለው የሰው እጣ ፈንታ በዳግም ውልደት በሚሽጋገሩበት ሂደት እንደሆነ ያስረዳል፤ነገርግን ጥቂት አይነተኛ ቡድሂስቶች ወደፊት የሚፈጥሩበትን ደረጃ ወይም ናንቫናን የማግኘት ኡደት ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ምክንያቱም ህይወታቸው ለመኖር በሚደረግ ትግል የተሞላ ነዉ።ሽልማትን የማግኘት ፍላጎታቸው የአሁኑን ህይወት ከማሻሻል ጋር የተያያዘ ነው።




ብዙ የቡድሂዝም ተፋላሚዎች ከዘላለም የካርማ ህግ ማንም ሊከልላቸው እንደማይችል ያምናሉ። ምክንያቱም ያለፈው የህይወት ሁነት የአንድን ሠው የጭንቅ ደረጃ ይፅፋል።



በ40ቀን እድል ማመናቸው ብዙዎችን በብዙ መናፍስት መኖር እያመኑም ቢሆን የቡድሂዝም እምነት እንዲከተሉ ያደርጋቸዋል። ከቡድሂዝም ፍልስፍና ስር ማለትም አምላክ አለመኖሩንና የሠው ነፍስ አለመኖሩን ቢያስተምርም ብዙ ቡዲህስቶች ግን የጥንት የመናፍስት እምነቶቻቸውን ደብቀው በፍርሃት ይኖራሉ።

ትርጉም ፦ ምህረት በቀለ
ምንጭ ፦ Wikipedia.com
Joshua.org



# ዶ/ር ዶን ሪቻርድሰን
# ከሰኔ 23, 1935 - ህዳር 23, 2018
# የእርቅ ህጻን

ለወንጌሉ ምቾቶቻችንን ለቀን ለመሄድ የተዘጋጀን እካልሆንን ድረስ ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ ሰራተኛ መሆን የህይወታችን ከባዱ ስራ ይሆናል። ከብሉይ እስከ አዲሱ ኪዳን የምናገኛቸው የዕምነት ሐዋርያዎች ህይወታቸው ራሳቸውን ሳይሆን እግዚአብሔርን ለማሳየት የተለየ፣ ከአለም ብልጭልጭ ለእግዚአብሔር መከራን መቀበል የመረጡ እንደሆነ እንመለከታለን።

ታሪክ ከማይረሳቸው የወንጌል አርበኞች ፊት አውራሪ ከሚቀመጡትይመደባል ዶ/ር ዶን ሪቻርድሰን። በወንጌል አገልግሎት ውስጥ ለማገልገል ያለው ናፍቆት ከልጅነት አብሮት ያደገ ነበር ይህንም ዶን ሲናገር " በልጅነቴ የቤተሰቦቼ ማሳ ላይ ብዜ ግዜ አሳልፍ ነበር፤ ብዙ ሰዎችም ወደዛ ይመጡ ነበር ። የሚመጡት ሰዎችም አንድ ጥያቄ ይጠይቁኝ ነበር ስታድግ ምን መሆን ትፈልጋለህ የሚል? እኔም አላውቅም እላቸዋለው። ይህ ጥያቄ ሲበዛብኝ አንድ ምሽት የመኝታ ክፍሌ መስኮት ጋር ተንበርክኬ እንዲህ ጸለይኩ፤ እግዚአብሔር ሆይ ሳድግ ምን መሆን እንደምፈልግ አላውቅም ሁሉም ሰዎች ደግሞ ስታድግ ምን መሆን ትፈልጋለህ ብለው ይጠይቁኛል ይህን እነዳውቅ እርዳኝ አልኩ እና ተነሳሁ። ይህን ጸሎት ካደረኩ በኃላ በሳምንቱ ከቤተሰቦቼ ጋር ፕሮግራም በምንካፈልበት ቤተክርስቲያን አንድ ሚሲዮናዊ ኢስያ ውስጥ ስለነበረው አገልግሎት ይናገራል እኔም የዚያቀን ወደ ፊት ምን መሆን እነደምፈልግ አወኩ። የት እና መቸ ይሁን አልገባኝም ግን ሚሲዮናዊ ሆኜ እንደምሄድ ግን እርግጠኛ ሆንኩ"።
ይህን
ጥሪ ለማስተናገድ እና ለተልዕኮ ለመዘጋጀት ጀን በፓአራሪ መጽሐፍ ቅዱስ ተቋም እና በቋንቋ ጥናት ተቋም (Prairie Bible Institute and the Summer Institute of Linguistics) ትምህርቶችን በመውሰድ በ 1962 ከባለቤቱ ካሮል እና የሰባት ወር ህጻን የሆነው ልጃቸውን ይዘው ሳዊ የሚባል የህዝብ ክፍልን ለመድረስ ፓፑ ዋ ኒው ጊኒ ወደ ተባለ ቦታ አቀኑ። የሳዊ ህዝቦች ካኒባሊስት፣ በአደን ፣በደፈጣ ጠላትን በማጥቃት፣ እና የቀሉት ጭንቅላት እነደ ጀግንነት መለያ የሚያዩ ነበሩ።

የሳዊ ህዝቦች የሚሲዮን ተቋማት ህበረት ሚሲዮናውያን እንዲገቡባቸው ፍቃድ እና ይሁንታ ከሰጠባቸው የዓለም ክፍሎች ውጪ ይገኙ የነበሩና ማንም ሚሲዮናውያን እዲገባ የማይፈቀድባቸው ህዝቦች ነበሩ፤ በዚህ መልኩ ከእነርሱ ጋር አብሮ መኖር የማይታሰብ ፣ ለተለያዩ በሽታዎች የተጋለጡ እና የማያቋርጡ የጎሳ ውጊያዎች የነበሩበት ስፍራም ነበር። ዶን ግን ባለቤቱን እና ልጁን አደጋ ላይ እየጣለ እንደሆነ ቢያውቅም ለሳዊዎች ክርስቶስን ለመስጠት አቀና።
በግዜው የሳዊ ህዝብ መሪዎች ሌሎች ጎሳዎች ላይ የፊታቸውመልክ ሌላ የሆኑ ሰዎች የተለያዩ ለማህበረሰቡ መገልገያ የሚሆኑ ቁሳቁሶችን ፣ ህክምና እና ትምህርት ይዘው እየሄዱ እንደሆነ ይሰሙ ስለነበር ወደ እንርሱ የመጣው ይህ መልከ ልውጥ ሰው ሌሎቹ ጎሳዎች ላይ እንደሰሙት ያደርጋል ብለው ስላሰቡ ይህን ሰው እና ቤተሰቡን በመልካም አቀባበል አደረጉላቸው። ይህን አጋጣሚ ዶን ሲናገር እንዲህ ያስታውሳል " ከጀልባ ስንወርድ ጀምሮ በከፍተኛ ጭፈራ
እና ሆታ ተቀበሉን ከዚያ አንስትን ወደ ተዘጋጀው መኖሪያች እስክንደርስ ድረስ አጅበውን እየጨፈሩ ቤታችን አስገቡን ይህ ሳይበቃ ሙሉ ለሊት በቡታችን ዙሪያ እየተሽከረከሩ ሲጨፍሩ አደሩ ይላል"።
ቋንቋቸውን እየተማረ እና ከህዝቡ ጋር አብረው መኖር ከጀመሩ በኃላ የሳዊ ህዝቦችን እና የእርሱን የክርስቲያን ንጽረተ አለም የሚለያይበትን አንድ እውነት አገኘ ይህም በእነርሱ እይታ የወንጌል ጀግና ኢየሱስ ሳይሆን ይሁዳ ሆኖ አገኘው።

ኢየሱስ የሚሳቅበት ሞኝ እንጂ የሚሞገስ አለመሆኑን ! በዚህም በግዜ ሂደት ዶን ሪቻርድሰን "የትድግና ስነመለኮት" የሚል አንድ መረዳት አዳበሩ። ይህም መረዳት መጸሐፍ ቅዱስ ላይ ካሉት ምንባቦች በዘለለ ለሰው ልጆች ሐጢያት የሞተውን፣ የተነሳውን እና የተሰራልንን የቤዛነት ስራ ለዚህ ህዝብ የሚናገርበት መንገድ ነበር እርሱንም የእርቁ ህጻን ይለዋል።





<u>የእርቁ ህጻን</u>

በግዜው ሶስት ጎሳዎች በማያቋርጥ ውጊያ ውስጥ ነበሩ ። በዚህም የተሰላቹት ዶን ሪቻርድሰን እና ቤተሰቡ ለጎሳ መሪዎች ይህ ጦርነት እና ውጊያ ማብቂ ከሌለው ከዚያ እንደሚሄዱ ይነግሯቸዋል። የጎሳ መሪዎቹም በእነዚህ ሰዎች መኖር ያገኟቸውን ጥቅሞች በተለይም በባለቤቱ ካሮል አማካኝነት እያገኙ ያሉት የጤና አገልግሎት ትልቅ ዋጋ ነበረውና ከሌሎቹ ጎሳዎች ጋር እርቅ ለማውረድ ይስማማሉ። ታዲያ ለዚህ ህዝብ ለዘመናት ዝግ የመሰለው የወንጌል በር እንዲከፈት ምክኒያት የሆነው ይህ የእርቅ ስዓት ነበር።



እነዚህ ሶስት ጎሳዎች እርቅ ለማውረድ አንዱ ጎሳ ለሌላው ጎሳ ገና የተወለደ ህጻን ልጅ በመለዋወጥ ነበር የእርቁ ስርዓት ይፈጸማል፤ ይህን የተመለከቱት ዶን እጅግ ተደነቁ ይህንም አጋጣሚ በመጠቀም እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ከሐጢያት እና ዘላለም ሞት ለማዳን አንድያ ልጁን እንደሰጠ፤ በዚህ ለሰው ልጆች ስርየት በተሰጠ ህጻንም ሰው ከእግዚአብሄር ጋር እንደታረቀ ሲነግሯቸው ማህበረሰቡ ክርስቶስን ለመከተል የወንጌልን እውነት ለመቀበል ግዜ አልፈጀበትም ነበር።

ዶን ሲናገሩ ልዩ መገለጥ እና አጠቃላይ መገለጥን ለወንጌል ተልዕኮ እንዴት ማዋል እንዳለብን ቅድሚያ ልናሰስበው ሚገባ ጉዳይ ነው ይላሉ። እያንዳንዱ ባህል እና ህዝብ ስለ ፍጥረት፣ ሐጢያት፣ ደህንነት የራሱ መረዳት እና እውቀት አለው ይህ ለአንድ ማህበረሰብ ወንጌልን ለማድረስ ትልቅ እድል ሚከፍት በር ነው።



ከእርቁ በኃላ ብዙዎች ከሳዊ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ከሌሎቹም ህዝቦች ወደ እግዚአብሔር መንግስት ተጨመሩ ቤተክርስቲያን ተተከለች፣ ሰዎች እውነተኛ ደቀ መዝሙር ለመሆን ይታጠቁ ጀመር።

ዶን የሳዊ ህዝቦችን ቋንቋ ከተማረ በኃላ  የአዲስ ኪዳን የመፀሐፍ ቅዱስ ክፍልን፣ ሌሎች መንፈሳዊ መጽሐፎችን በመተርጎም እና በማዘጋጀት ለወንጌል ስራ ተጠቅሞበታል ከዚህም ባለፈ የቀለም ትምህርር ለመጀመር የሳዊን ቋንቋ ከንግግር ባለፈ ወደ ፊደልነት በመቀየር ትምህርት በመጀመር በማህበረሰቡ ውስጥ ብዙ ለውጦች እንዲመጣ ምክኒያት ሆኗል። ከዚህም በኃላ የሳዊ ቤተክርስቲያን የሐገሬው ሰዎች በሆኑ እንድትመራ በማድረግ በዚያው አካባቢ ያሉ የአዩ ህዝቦችን  ቋንቋ ወደ ፊደለ ለመቀየር እና ለማዘጋት ስራ ጀመሩ።

ወደ ገጽ 12 ዞሯል...

የዓለማችን ያልተደረሱ የሐይማኖት ክፍሎች

# ሐይማኖት የለሽ

አጠቃላይ የእምነቱ ተከታዮች

- 982,497,000 -

አለም አቀፍ የህዝብ ብዛት

በ% ሲሰላ

- 12.9 % -

የሚገኙበት የህዝብ ክፍሎች

ብዛት

- 259 -

ያልተደረሱት የህዝብ

ክፍሎች

- 19 (7.3 %) -

# ሀይማኖት የለሽ ህዝቦች

በ2012 የአለም አቀፉ ፒው የጥናት ማህከል መረጃ እንደሚያሳየው ። 16% የዓለም ህዝብ ከሀይማኖት ጋር ያልተያያዘ ሲሆን 84% ደግሞ ከሀይማኖት ጋር የተያያዘ ነው ።
ሀይማኖት የለሽነት ብዙ ንዑስ ክፍሎች ያሉት ሲሆን ከግዴለሽነትና አለማወቅ ጀምሮ ሠው ብቻ እስከሚለው አለማዊ ፍልስፍና የሚደርሱ ናቸው። ከንዑስ ክፍሎቹ መሀል ኤቲዝም፣ አግኖቲዝም፣ አንቲቲህዝምና ሌሎችም ይገኙበታል።
በተግባራዊነት ሀይማኖት የለሽ መሆን በማህበራዊ ሳይንስ ከለላ ንፁህ ተፈጥሮአዊ የሆነ የአለም ዕይታ ወይም ያለ ልዕለ ተፈጥሯዊ ሀይል ጣልቃ ገብነት መከተል መቻል ነው። ሰፊው ትርጓሜ ሀይማኖታዊ የሆነ ማንነትን ማጣት መቻል ነው። በዚህ ማንነት ማጣት ውስጥ ብዙ ሜታፊዝካል እምነቶች፣ ጠባብና ጥብቅ አምላክን የመካድ ሀሳቦች ይስተዋላሉ። የሀይማኖት የለሾች አለም የህዝብ ጥናት ካለፈው ከፍተኛ ብዛትና ቀጣይ ዝቀተኛ ብዛት ተነስቶ ይሰራል። ስለዚህ ከ450 ሚሊዮን እስከ 1.6 ቢሊዮን ሠዎች ይገኙበታል። በተለይ ከምዕራቡ ውጪ ባለው "ሀይማኖት " ና "አለማዊነት" በስልጣኔው ውስጥ ባልሰደደበት አለም በስፋት ይገኛል።
የሀይማኖት የለሽነት የተለያዩ ክፍሎች

ኤቲዝም፦ የአማልክት መኖርን የሚቃወም እምነት ነው። ከአሉታዊ እስከ አዎንታዊ ኤቲዝም ሰፊ ልዩነት አለ።

ዲኢዝም፦ የፍልስፍና እምነት ሲሆን ለሀይማኖት እውቀት መገለጥ ምንጭ
መሆን እንደማይችል ይገለፃል ለህዋ ፈጣሪ ወይም ልዕለ ተፈጥሯዊ ሀይል መኖሩን ለማረጋገጥ ምክንያታዊነትና ማስተዋል በቂ እንደሆነ
ይገለጻል ።

አግኖቲዝም፦ የፈጣሪ መኖር ወይም የመለኮታዊ እና ልዕለ ተፈጥሯዊ ሀይል
መኖር ሊታወቅ አይችልም የሚል እይታ ነው።

አግኖስቲክ ኤቲዞም፦ ኤቲዝምንና አግኖቲዝምን በአንድ ላይ ያቀፈ የፍልስፍና እይታ ነዉ። አግኖስቲክ ኤቲስቶች በአምላክ መኖር አያምኑም ምክንያቱም የፈጣሪ መኖር ወይ አይታወቅም አልያም አይረጋገጥም ።

አፖቲዝም፥ በፈጣሪ መኖርና አለመኖር ላይ ምንም ፍላጎት አለማሳየት
ናቹራሊዝም፦የተፈጥሮ ህግና ሀይላት ብቻ ህዋን እንደሚያንቀሳቅስ
ማመን (ከልዕለ ተፈጥሯዊ እና መንፈሳዊ ሀይላት በተቃራኒ )

አንቲ ሪሊጅን፦ ማንኛውንም አይነት ሀይማኖት መቃወም

ሴኩላሪዝም፦ የራስ ሃይማኖተኝነት በማስወገድ ፖለቲካን እና ሀይማኖትን ለመለየት የሚሠነዘር ሀሣብ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ በተለይ በአሜሪካ ውስጥ የናቹራሊዝምና ኤቲዝም መገለጫ ምልክት ነው።

ሴኩላር ሂዩማኒዝም፦ ከመለኮታዊ ሀይል በላይ ሠውን ማስበለጥን የሚያጎላ እምነት ነው። ፀረ አምላካዊ ሀይማኖት ከባህላዊ ሀይማኖት ተቃራኒ መሆኑን የሚገልጽ ሠዋዊ ፍልስፍና ነው።

ፍሪቶት፦ እውነት ከምክንያት፣ አመክናና ልማዳዊ ሀቅ ላይ እንጂ በስልጣን፣ በባህል፣መገለጥና ሌሎች ቀኖናዎች መመስረት የለበትም።

ቲዎሎጂካል ነን ኮግኒቲቪዝም፦ የሀይማኖት ቋንቋዎች በተለይ "እግዚአብሔር
"የሚለው ቃል በአእምሮ ስናስበው ትርጉም የለውም ወይም የአምላክን መኖር ማወቅ አይቻልም ብሎ ማመን ነው።

መንፈሳዊ ግን ሀይማኖታዊ ያልሆነ፦ ባህላዊ ወይም የተደራጀ ሀይማኖት ለብቻው መንፈሳዊ እድገትን ለማምጣት ወሳኝ አይደለም ብለው ለሚያምኑ ሰዎች ልዩ መጠሪያቸው ነው። ኤሰ.ቢ.ኤን.አር በሀይማኖት የለሽ ስር ይካተታል። ግን ደግሞ
ለብቻው ይቀመጣል።

# ሀይማኖት የለሽ ህዝቦች

## የህዝብ ጥናት

ከዚህ በታች የተጠቀሱት 11 ሀገራት በሀይማኖት የለሽነት ከፍተኛውን ቦታ ይይዛሉ። ይህ ማለት ግን የሀገሪቱ አብዛኛው ህዝብ የትኛውንም ሀይማኖት የማይቀበል ነው ማለት አይደለም ። ለምሳሌ የስዊድን 58% ህዝብ ሉተራን ቤተክርስቲያን አባል ነው ። የስካንዲኒቪያን ሀገራት በሀይማኖት የለሽነት ከፍተኛ ቦታ ቢይዙም ኤቲዝምን ጨምሮ በአውሮፓ 47% ኤቲስቶች የሀገር አቀፋዊ ቤተክርስትያን አባል ናቸው ።

የሀይማኖት የለሽነትን አላማ መለየት ከሃይማኖታዊ እና አለማዊ ፅንሰ ሀሳብ አኳያ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ህብረተሰብ ባህላዊ ትብነትን ይጠይቃል። በተለይ ደግሞ "ሀይማኖታዊነት" እና "አለማዊነት" ስልጣኔ ስር ባልሰደደባቸው ከምዕራቡ ውጪ ባሉት ሀገራት ብዙ የኤዠያ (ውዞንግጂአ -በቻይና, ሙሽኩዬ-በጃፓን) በዛ አግባብ ሀይማኖት ስንል ቡዲዝም ወይም ክርስትና ማለታችን ነው፤ ብዙ ሀይማኖት የለሾች "ሺንቶን"ወይም ሌላ የባህል አምልኮዎችን ይከተላሉ። በሙስሊሙ አለም ሀይማኖት የለሽ "ሺንቶን" ወይም ሌላ የባህል አምልኮዎችን ይከተላሉ። በሙስሊሙ አለም ሀይማኖት የለሽ መሆን ማለት እስልምናን በአግባቡ አለመከተል ነው። በእስራኤል አለማዊ ማለት ጥብቅ የሆነ አይሁዲነትን አለመከተል ነው። በተገላቢጦሽ በአሜሪካ ያሉ ይሁዲዎች ሀይማኖት የለሽ ከአይሁዲነት አለመከተል ነው። በሩሲያ የምስራቃዊ ኦርቶዶክስ መለያን ማሳደግ ባህላዊና ሀገራዊ ህሳቤን ከግምት በማስገባት ነው። ስለሃይማኖትና ሀይማኖት የለሽ በፒው በ2015 የተደረገው ጥናት ከ2010-2050 የማይታመን የቁጥር መጨመር በ2050 በቁጥር ማሽቆልቆል ይተካል ብሎ ይገልጻል።

ሶሾሎጂስት ፊሊ ዛከር ኤቲዝም ላይ ያደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው ኤቲዝም በሀይማኖት የለሽ የውልደት መጠን መቀነስ ምክንያት ሊመናመንና ሀይማኖትን የሚከተሉ ሀገራት የውልደት መጠን መጨመር ሀይማኖትን ሊያጎለብት ይችላል። ሀይማኖት እና የህዝብ ቁጥር ተቃራኒ ግኑኝነት ስላላቸው በ21ኛው መቶ አመት ሀይማኖት የለሽነት እንደሚዳከም ይገመታል። እንደ ፒው ፕሮጀክት የአላማኝ ቁጥር በ35 ሚሊዮን ሲጨምር በ13% ደግሞ በፍጥነት እያሽቆለቆለ ይመጣል።

እንደ ፒው የ2012 አለም አቀፋዊ ጥናት 230 ሀገራት 16% ህዝባቸው ሀይማኖትን የሚከተል አይደለም, 84% ደግሞ ሀይማኖትን ይከተላል። የ2012 አለምአቀፋዊ በራሱ የሚመራ ኔትወርክ ጋል አፕ አለምአቀፋዊ ማህበር ሪፖርት እንደሚያሳየው 57 ሀገራት 59% ህዝብ ሀይማኖትን የሚከተል ሲሆን፣ 23% ሀይማኖት የለሽ ፣ 13% ያመኑ ኤቲስቶች ፤ በ2005 ዓ.ም ከ39 ሀገራት ጋር ሲነፃፀር ሀይማኖታዊ ተብሎ መለየት ያልተቻለ 9% ሊገኝ ችሏል። የፒሎ 2015 ክትትል እንደሚያሳየው 63% የአለም ህዝብ ሀይማኖትን የሚከተል ፣ 22% ሀይማኖት የለሽ፣ 11%ያመኑ ኤቲስቶች ናቸው። የራሳቸው ሪፖርት እንደሚያሳየው 62% ሀይማኖትን የሚከተሉ 25% ሀይማኖት የለሽ፣ 9% ያመኑ ኤቲስቶች ናቸው ይሁንና ሌሎች ጥንታዊ ፅሁፎች የዊን ጋል አፕ አለማቀፋዊ ምስልን ለመቅረፅ ሲሞክሩ ቆይተዋል።ከዛ በመቀጠል የተለያዩ ጥናቶች ለብዙ አስርት አመታት ሲያዘጋጁ ቆይተዋል። ከዛ በመቀጠል የተለያዩ ጥናቶችን ለብዙ አስርት አመታት ሲያዘጋጁ ቆይተዋል። የአለም የህዝብ ጥናት ከፍተኛ ናሙና እንደሚያመለክተው በአለም ውስጥ ያሉ ኤቲስቶች ቁጥር ዝቀተኛ መሆኑን ነው።

ትርጉም :- ምህረት በቀለ
ምንጭ :- Wikipedia.com
Joshua.org

ከገጽ 9 የቀጠለ....


በ1977 እ.አ.አ ዶን እና ባለቤቱ ወደ ሰሜን አሜሪካ በመመለስ ወርልድ ቲም (World Team) የተባለ አገልግሎት በማቋቋም በሰፊው ማገልገል ጀመረ። በፓሲዲና በሚገኝ የሴንተር ፎር ወርልድ ሚሽን (U.S Center for World Mission) አገልግሎት ትምህርት ቤትም ዳይሬክተር ኦፍ ትራይባል ፒዩፕል ስተዲስ (Director of Tribal Peoples' Studies) ማስተማር ቀጠለ። የፕርስቴክቲቭ ኦን ዘ ወርልድ ክርስቲያን ሙቭመንት (Perspectives on the World Christian movement) የተሰኘ የተልዕኮ ትምህርት እንዲዘጋጅ እና ለማስተማሪያነት እንዲውልም ብዙ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ዶ/ር ዶን ሪቻርድሰን ከዚህ ባለፈ በጻፏቸው መጽሀፎች ብዙዎችን መድረስ የቻሉ እና ለብዙዎችን ለወንጌል አገልግሎት ለመነሳት ምክኒያት ሆኗነዋል። መጽሐፎቹን እንደሚከተለው ከታች በእንግሊዘኛ ስያሜያቸው አስቀምጬላችኋለው። ነጻ ከሆኑ ድህረገጾች ላይ አብዛኞቹ ስለሚገኙ አውርዳችሁ እንድታነቡ ግብዣዬ ነው።


- Peace Child (1972)
- Peace Child (1975) ISBN 0-8307-0415-9
- Peace Child (2007) ISBN 1-57658-289-2
- Lords of the Earth (2003) ISBN 1-57658-290-6
- Eternity in Their Hearts: Startling Evidence of Belief in the One True God in Hundreds of Cultures Throughout the World (1981) ISBN 0-8307-3837-1
- Secrets of the Koran (2008) ISBN 0-8307-3123-7
- Unhidden (2009) ISBN 1-6079-1245-7
- Heaven Wins (2013) ISBN 0-7642-1559-0
- A Man From Another World (2016) ISBN 978-1-941733-74-5

እ.አ.አ 2012 ዶ/ር ዶን ሪቻርድሰን እና ሶስት በሳዊ ህዝብ መካከል የተወለዱ ልጆቻቸው ጋር በመሆን ወደዚህ ህዝብ የሄዱበትን የ50ኛ አመት መታሰቢያ ለማድረግ ተጉዘው ነበር። በዚህም ወቅት ከአምስት ጎሳዎች በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ወንጌልን ይዞላቸው የሄደውን ሰው እና ቤተሰቡን በብዙ ሆታ እና ጭፈራ ለመቀበል ተዘጋጅተው ነበር።







ከሃምሳ አመት በፊት እነዚህ ሰዎች መታወቂያቸው አንገት መቅላት፣ አዳኞች እና ነፍሰ ገዳይ መሆናቸው ነበር ዛሬ ግን ታሪኩ ሌላ ነው በእነዚህ ህዝቦች መካከለ ያ ደም አፋሳሽ ጦርነት የለም እንደውም እ.አ.አ በ1972 ዓ.ም አምስቱን ጎሳዎች ያማከለ ቦታ ላይ በህብረት ለማምለክ የሚችሉበት በጣም ትልቅ እስከ 30,000 ሰው ድረስ የሚያዝ አዳራሽ ገንብተዋል።




መታወቂያቸው ወንጌል፤ ማሰሪያቸው ፍቅር ሆኗል። ወንጌሉን ይሰብካሉ በዚህ በ50ኛ ዓመት መታሰቢያ ቀን ላይ 200 አዳዲስ ጥንዶች በክርስቲያናዊ ስርዓት በቤተክርስቲያን ፊት ቃልኪዳን አስረዋል፣ ኢየሱስ ክርስቶስን የህይወታቸው ጌታ አድርገው የተቀበሉ ከ18,000 በላይ አዳዲስ አማኞች የውሃ ጥምቀት ስርዓት ፈጽመዋል።

ከዚህ ሁሉ አስደናቂ የወንጌል ታሪክ ጀርባ ከ9 ዓመቱ ጀምሮ ሚሰዮናዊነትን እየናፈቀ ያደገ ደግሞም እግዚአብሔርን ታዞ ወደ እነዚህ ህዝብ ሚሲዮናዊ ሆኖ የሄደ ዶን ሪቻርድሰን፣ ይህን የወንጌል ሸክም ተቀብላ ከእርሱ ጋር አብራ ሚሲዮናዊ የሆነች ባለቤቱ ካሮሊን በብዙ ምናነሳቸው ናቸው።




እ.አ.አ ህዳር 23, 2018 ዓ.ም ይህ የወንጌል አርበኛ
የምድራዊ ሩጫውን ጨርሶ በክብር ወዳገለገለው ጌታው ለመሄድ አንቀላፋ። ሰማይ ይህ ጀግና ምን የተባለ ይመሳላቿጋል? እኔ ግን ሳስብ እግዚአብሔር ይህን ጀግና ልጁን ሲያይ አንተ በጎ ባሪያ ና ወደ እረፍት ግባ ያለው ይመስለኛል።
ብዙዎች ምድር የሚያውቀው ኑሮ ለመኖር ይታገላሉ ብልሆች ግን ብል በማይበላው መዝገብ ላይ የሚጻፍ ሰማይ ያወቀውን ኑሮ ለመኖር ይጥራሉ፤ አለም ሞኝ ይላቸዋል ሰማይ ሲደርሱ ግን በአክሊል የታጀበ ሽልማት ይጠብቃቸዋል።
"ጌታሆይ ቀድሞ ወንዝ በወረደበት ቦታ ሁሉ ወንጌልህ እንደገና ይፍሰስ "

ሊዚህ ወንጌል ለመኖር ጌታ ይርዳን !!
አማኑኤል ገዛኸኝ
የተልዕኮ አስተማባሪ
ጭማሪ ጽሑፎች ፡- Wekipdea.com
: - Mission Frontier

# ሀይማኖት የለሽ ህዝቦች
# ክፍል 1

በዓለም ላይ በአስር አርባ መስኮት ውስጥ ካሉ ካልተደረሱ አምስቱ የህዝብ ክፍሎች ውስጥ አንደኛው ናቸው።ሀይማኖት የለሾች፤ እስልምና ፣ የጎሳ ሐይማኖት፣ ሂንዱይዝም፣ ቡድሂዝም ሌሎች በዓለም ላይ ያሉ ያልተደረሱ የህዝብ ክፍሎች ናቸው ። ከአመታት በፊት በተሰራው ጥናት በዓማችን ላይ 121 ሚሊዮን ሀይማኖት የለሽ ሰዎች በአስራ አምስት የህዝብ ክፍሎች ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን ፤ ለእያንዳንዱም 1 ሚሊዮን ሀይማኖት ለሌላቸው ሰዎች 12 የወንጌል ሰራተኞች አሉ። ከላይ የተጠቀሰው ቁጥርም በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመር ላይ ይገኛል ። ይህም ሊሆን የቻለበት ዋነኛው ምክንያት በ21ኛው ክፍለ ዘመን እየተቀነቀነ ያለው የድህረ ዘመናዊነት እንቅስቃሴ የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል ።

የሰው ልጅ አብሮ መኖር ከጀመረባቸው እልፍ አመታት ጀምሮ ሀይማኖታዊ ይዘት ያላቸውን የተለያዩ የአምልኮ ስርዓቶች ሲከተል የኖረ ሲሆን በእዚህ ጊዜያትም ቢሆን ሀይማኖት አልባነት ለሰሚው እንግዳ የሆነ ነገር ነበር ።ቲሞቲ ኬለር ካውንተርፊት ጋድስ (counterfeit gods) በሚለው መጽሀፋቸው ውስጥ እንዳሰፈሩልን ሰው የተፈጠረው ለማምለክ በመሆኑ ማንም ሰው አምለኪ እንደሆነ እና ልዩነቱም ያለው ማንን ነው የምናመልከው? የሚለው ሀሳብ ላይ እንደሆነ ይነግሩናል ። ይህም አምልኮ ሀይማኖት የለሽ የሆኑትንም ይጨምራል ማለት ነው። ሀይማኖት የለሽነት ከዘመነ አብርሆት( Enlightenment ) ; የአመክንዮ አስተሳሰብ ጋር አብሮ በማበብ ላይ የነበረ እምነት ነው። ‹ ሰው በሚያስበው እና በሚያገናዝበው ምክንያት በዙሪያው ያሉትን ነገሮችም መረዳት ይችላል:: የኋላቀርነት መንስኤው የሰው ልጅ የአስተሳሰብ ዝግመት ሲሆን ይህን ድክመቱንም ለማካካስ ሲል ያበጃቸውን የእምነት ካባዎችን አውልቆ መጣል ከቻለ የማያቋርጥ እድገት ውስጥ መገኘት እንችላለን› የሚል አቋም ነበራቸው። ፍሬድሪክ ኒቼ ‹እግዚያብሄር ሞቷል› ብሎ ካወጀበት ጊዜም ጀምሮ ሰዎች የእግዚያብሄርን መኖር በመካድ የመጨረሻ የስልጣን ምንጭ እግዚያብሄር እና ቅዱስ ቃሉ ሳይሆኑ ሰው እና ሰው ብቻ እንደሆነ በማመን ብዙዎች እንቅስቃሴውን ተቀላቅለዋል። በመቀላቀልም ላይ ይገኛሉ ።

ከዚህም ባለፈ ዘመኑ የእግዚያብሄርን አለመኖር እልህ በተሞላበት ቁጣም የሚያስተምሩ የ21ኛ ክፍለ ዘመን አስተማሪዎች በቁጥር በርክተው የመጡበት ጊዜ ነው። ከነዚህም መሀል ሳም ሀሪስ ፤ ክርስቶፈር ሂችንስ፤ እና ሪቻርድ ዶውኪንስ ይታወቃሉ ።

በመጽሀፋቸውም መጽሀፍ ቅዱስን በማጣመም ሰዎች አይናቸውን ከእግዚያብሄር ላይ እንዲያነሱ ይታገላሉ። በቅርብ አመታትም ከፍተኛ ተደማጭነትን እያገኘ የመጣው የአይሁድ ዝርያ የነበረው አሜሪካዊው ጸሀፊ ዩቫል ሃራሪ በተከታታይ ባወጣቸው ሆሞ ሳፒየንስ እና ሆሞ ዲዩስ በተሰኙት መጽሀፎቹ እንዳብራራው ሰዎች ከእንስሳት በተለየ ሁኔታ በመተባበር የሚኖሩ ሲሆን አፈ ታሪክን የመፍጠር እና ያንንም አፈ ታሪክ እንደ እምነት በመውሰድ ጽንፍ ውስጥ በመግባት ማህበረሰብን የመፍጠር አቅም ስላላቸው ነው ላለፉት አመጣት በህይወት መቆየት የቻሉት ይለናል ። ሀይማኖትም ቢሆን የሰዎች የአስተሳሰብ ውጤት ነው በማለት ይሞግታል ። የእግዚያብሄር መሞትም በእርሱ ቦታ ያለውን የስልጣን ክፍተት በሂውማኒዝም በመተካት ሰውን የአምላክነት ደረጃ ላይ ያስቀምጠዋል። ሆሞ ዲየስ ትርጉሙ አምለካዊው ሰው የሚል አንድምታ ሲኖረው ፤ በመጽሀፉም በ21ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻም የሰው ልጅ በሽታን፤ ህመምን እንዲሁም ሞትን ድል ይነሳል የሚል መላምትን ያስቀምጣል ። ምንም እንኳ ጣዖታት የሰው ልጅ አስተሳሰብ እና ባህል ውጤቶች ቢሆንም እግዚያብሄርን ከዚህ ጎራ መመደብ ግን ሞራላዊ እና ህሊናዊ የሆነው ህግ የሚጥስ ሰውንም በምትኩ አምላክ አድርጎ የሚሾም ድርጊት ነው።

የሰው የመኖሩ ትርጉም ያለው እምነቱ ላይ ሲሆን ፤ እግዚያብሄርን በሂውማኒዝም ፍልስፍና መቀየሩ የፈጠረው እግዚያብሄር ብቻውን ሊሰጠው የሚችለውን የመኖር ትርጉም እንዲያጣው ያደርጋል ። ያለ እግዚያብሄር የመኖር ትርጉም በግል ምልከታ ላይ የተመሰረት እሳቤ እንጂ ወጥ የሆነ አስተምህሮ ሊሆን ባለመቻሉ ምክንያት በዓለም ላይ ክፍተኛ የሆነ የግለኝነት( Individualism) አብዮት በመፈንዳት ላይ ይገኛል ። ይህ የህይወት ትርጉም ሰውን እንደሰው የሚያንቀሳቅሰው ዋነኛ መሳሪያ ነው ። አውግስቲን በታወቀው አባባሉ ‹ አንተ ለራስህ ስትል ፈጥረኸናልና ነፍሳችን አንተን እስክታገኝ ድረስ እረፍት የላትም › ብሎን ነበር። የዚህ እረፍት የማጣት ትልቁ ምልክት አንዱ ማሳያ የሚሆነን ነገር ባደጉት ሀገራት ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ያለው ራስን የማጥፋት ሙከራ ነው። እነዚህ ሰዎች የገንዘብ እጥረት የለባቸውም ፤ መሰረታዊ የሆኑትን ስጋዊ ፍላጎቶች አሟልተዋል ነገር ግን ራሳቸውን ‹በእግዚያብሄር ክፍተት› ላይ በማስቀመጣቸው ምክንያት ሊሞሉት ያልቻሉት ገደል ራሳቸውን እንደ ጥቁር ገደል ( Black hole) ጠቅልሎ ወስዷቸዋል:: ከላይ በዝርዝር ባስረዳነው ምክንያትም እነዚህን የህዝብ ክፍሎች ሀይማኖት የለሾች ብለን ከምንጠራቸው ይልቅ ራስን አምላኪዎች ብለን ብንጠራቸው ከአስተምህሮአቸው ጋር ይበልጥ እንተዋወቃለን ብዬ አስባለው። ራስን የማምለክ አመለካከት የሚከተሉ የህዝብ ክፍሎች በሁለት ጎራ ተከፍለው የሚኖሩ ናቸው ።

1. የመጀመሪያዎቹ ጽንፎች መልከዓ ምድራዊ በሆነ ክፍፍል ብናያቸው ምዕራባውያን ተብለው ሲጠሩ በሰሜን አሜሪካ፣ በአውሮፓ እና ሊበራል በሆኑ ሀገራት ውሰጥ የሚኖሩ ናቸው ። እነዚህ አምላኪዎች የሚከተሉት ፍልስፍና ግለኝነት (Individualism) ላይ የሚያጠነጥን ሲሆን። እያንዳንዱ ሰው የፈለገውን ነገር የማድረግ እና የሚመርጠውን የህይወት ስርዓት እንዲከተል የሚያበረታቱም ናቸው ። ‹ አንተን ደስ የሚያሰኝህ ከሆነ አድርገው › የሚል ሞራላዊ መፈክር ሲኖራቸው የአንድ ነገር መልካምነት ወይም ክፋት የሚወሰነው አንድ ሰው በነገሩ ላይ በሚኖረው ስሜት ላይ ነው ሲሉም ይደመጣሉ። መዝፈን ደስ ካሰኘህ ዝፈን ፤ ተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት ካስደሰተህ አድርገው ፤ መጠጣት ካስደሰትህ ጠጣ እና የመሳሰሉ አቋሞቸን ያለፍርሀት ያንጸባርቃሉ ። ሰዎች ላይም ክፉ ነገር የማያደርጉት ለህሊና ህግ ተገዝተው ሳይሆን ድርጊታቸው በሌላ ሰው ላይ መልካም ያለሆነ ስሜት ስለሚፈጥር ብቻ ነው።የዚህ እሳቤ አካሄድ ዓለምን ወደ ለየለት ቀውስ ውስጥ እንዳይስገባትም ብዙዎች ይሰጋሉ ። በዚህ ሰዓትም አሜሪካ እንደ ሀገር እንዳትቆም ካደረጉ ብዙ ምክንያቶች ውስጥ በዋናነት እየተጠቀሰ የሚገኘው ጉዳይ ራስን ከመጠን በላይ የማላቅ እና አምለካዊ ባህሪን የማላበስ ልምምድ እንደሆነ ከሀይማኖት አስተማሪዎች እስከ ፖለቲከኞች፤ ከጋዜጠኞች እስከ ነጋዴዎች ይህ ሀሳብ እያስገነዘቡን ይገኛሉ።

2. ሁለተኛው ጽንፍ የምዕራባውያንን የግለኝነት አካሄድ በመቃወም ማህበራዊ ልህቀት የሚያምኑ የህዝብ ክፍሎች ናቸው። እነዚህ የህዝብ ክፍሎች በአብዛኛው የሚገኙት በሩቅ ምስራቅ ኤሽያ ንፍቀ ክበብ ውስጥ ነው ። ሰሜን ኮሪያ ፤ ቻይና እና ጃፓን ( በጥቂቱ ) አክራሪ የሆነ የሶሻሊት አስተሳሰብን የሚያራምዱ ሲሆን እሳቤያቸውም ለሁሉም ሰው ያልተገደበ ነጻነት የሚሰጥ ከሆነ ስርዓት አልበኝነት ገደቡን ጥሶ ይወጣል ስለዚህም ግለኝነት ገደቡን እንዳይጥስ ከህዝቡ የተውጣጡ ልህቀት ያላቸው አመራሮች በሚያወጡት መርህ ብቻ መመራት አለብን የሚሉ ናቸው። ምንም እንኳ ይህ ጽንፍ መልካም ጎን ያለው ቢመስልም የመጨረሻውን የስልጣን እርከን ለእግዚያብሄር ሳይሆን ህዝቡን ለሚያስተዳድሩት አካላት ነው የሚሰጠው ።በሰሜን ኮሪያ ኪም ጆንግ ኡን የሁሉ ነገር ፈላጭ ቆራጭ ፤ ከጥቂት አስርት አመታት በፊትም ማኦ ዜ ዶንግ በቻይና ለአምላክነት በቀረበ ፍርሀት ህዝቡን ሲመሩ ነበር የቆዩት:: በነዚህ ሀገራት እንደ ቅዱስ ቃል በየቤቱ የሚነበበው የሚጠናው መጽሀፍ መሪዎቹ ያዘጋጁት በልዩ መጠሪያ የሚጠራው ህገ መንግስቱ ሲሆን ማንም ሰው ከነዚህ መጽሀፍት ውጪ ምንም አይነት ሀይማኖት እንዲከተል ፈጽሞ የተፈቀደም አይደለም ።
ነገሮችን ለማጠቃለልም እኛ ክርስቲያኖች ሁለቱንም ሀይማኖት የለሽ ጽንፎች በመረዳት አወዱን በጠበቀ መልኩ ወንጌልን ለነዚህ ሰዎች የማድረስ ሀላፊነት ያለብን ሲሆን፣ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈላቸው ደብዳቤው እንዲህ የሚል አቋም ነበረው። የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን 2 ቆሮ 10:5 የሀዋርያቱን ፈለግ በመከተል አዕምሮን ሁሉ ለክርስቶስ የምንማርክበት ዘመን እንዲሆንልን ጸሎቴ ነው ፤ በሚቀጥለው ዕትምም እነዚህን የህዝብ ክፍሎች እንዴት መድረስ እንደምንችል በስፋት የምንዳስስ ይሆናል።

ሐኖክ ፍታኔ
የተልዕኮ አስተማባሪ


የዓለማችን ያልተደረሱ የሐይማኖት ክፍሎች
የጎሳ እምነት ተከታዮች
አጠቃላይ የእምነቱ ተከታዮች
- 721,743,000 -
አለም አቀፍ የህዝብ ብዛት
በ% ሲሰላ
- 9.5 % -
የሚገኝበት የህዝብ ክፍሎች
ብዛት
- 2,642 -
ያልተደረሱት የህዝብ
ክፍሎች
- 2,375 (91.5%) -

# የጎሳ እምነት



የጎሳ ዕምነት ተከታዮች በዓለማችን በሚገኙ 70 ሀገራት ውስጥ ከ370 ሚሊዮን በላይ ሰዎችን ይዘው ይገኛሉ። እነዚህ ህዝቦች የራሰሳቸው ባህል፣ ቋንቋ፣ ወግ እና ስርዓቶች ያሏው ናቸው ይህም ከተቀረው ማህበረሰብ እና የዘመናዊነት ዓለም ርቀው እንዲገኙ አድርጓቸል።

የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከ3000 - 6000 ያልተደረሱ የጎሳ ዕምነት ተከታይ የሆኑ የህዝብ ክፍሎች እንዳሉ ሲሆን እነርሱም በአለም ዙሪያ ይገኛሉ። ለምሳሌ ፦ በአለም ላይ በተለያዩ ቦታዎች እንደ ኢራን ያጃ፣ ፓፑዋ ኒው ጊኒ ፣አማዞን ቤዚንና አፍሪካ አህጉር ውስጥ ይገኛሉ። በሳንፍራንሲስኮ ቴክሳስ የጎሳ ጥናት ተቋም ዳይሬክተር ዴቭ ሲተን እንደገለፀው በዓለማችን የሚገኙ 2,000,000 ዘላኖች የጎሳ እምነቶች ተከታይ ናቸው።



የጎሳ ህዝቦች ጥንታዊነት እና ከሰፊው ማህበረሰብ ተገሎ የሚኖር ታሪክ  ከውጪ የመጡ ሰዎችን እንዳያምኑ እና እንዲጠራጠሯቸው አድርጓል። የማይታወቁ መንፈሶች ፍርሀት አዲስ ግዛቶችንና ሀሣቦችን ከመፈለግ ያግዳቸዋል። ሚሲዮናውያን መቅረፍ ያለባቸው ትልቁ ችግር 'ጭነታዊነት'፦ የውጫዊነት ቀረቤታ ፣ፈረንጅ ፣ መሳሪያዎቹና ሀብቱን ነው።

ከ ዘጠና ሚሊዮን ህዝብ በላይ የት ነው ያሉት? ጥያቄው መሆን
ያለበት "የሌሉት የት ነው"። የጎሳና የዘር እምነት ከሞላ ጎደል በሁሉም ሀገር ውስጥ ይገኛል። ብዙሃንኑ ግን በአፍሪካ አህጉር ይገኛሉ። ሌሎች ትላልቅ ቡድኖች ደግሞ በቻይና ፣ኢንዶኔዥያ ፣ላኦስ ፣ማሌዥያ ፣ፊሊፒንስና ብራዚል ውስጥ ይገኛሉ ።

ተግዳሮቶች? ብዙ የጎሳ ሀይማኖቶች ለመናፍስቱ እርካታ የሚያቀርቡት በመስዋት እና በበአላት ነው። ይህም ከህይወታቸው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነትና ተፅዕኖ እንዳለው ያምናሉ ብዙ ጊዜ የተለየ ቋንቋ አላቸውና በራሳቸው ቋንቋ መፅሀፍ ቅዱስ የላቸውም። በአካል ለማግኘት ከባድ የሚያደርጋቸው በተገነጠለ ጥንታዊ ቦታ መኖራቸው ነው።



እንዴት ልፀልይላቸው እችላለሁ? ለመፅሀፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ፀልዩ ወደ 340 ሚሊዮን ሠዎች በራሳቸው ቋንቋ መፅሐፍ ቅዱስ የላቸውም። የጎሳ ህዝቦች በመንፈስ ፍርሀት ውስጥ ይገኛሉ። በክርስቶስ በኩል ነፃነትን እንዲያገኙ ፀልዩላቸው።

ትርጉም ፦ ምህረት በቀለ
ምንጭ ፦ Wikipedia.com
Joshua.org

የዓለማችን ያልተደረሱ የሐይማኖት ክፍሎች

# እስልምና

**አጠቃላይ የእምነቱ ተከታዮች**

**- 1, 792,955,000 -**

**አለም አቀፍ የህዝብ ብዛት በ% ሲሰላ**

**- 23.6 % -**

**የሚገኝበት የህዝብ ክፍሎች ብዛት**

**- 3,620 -**

**ያልተደረሱት የህዝብ ክፍሎች**

**- 3,067 (84.7%) -**

# እስልምና

ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ610 A.D. በአንድ ማታ "መሀመድ አንተ የአላህ መልእክተኛ ነህ።" የሚል ራእይ ወደ መሀመድ መጣ። ይህም የእስልምና ሀይማኖትም ጅማሮ ሆነ።
"እስላም" የሚለው ቃል "መገዛት" ማለት ሲሆን ፤ "ሙስሊም" የሚለው ደግሞ "ለአላህ የተገዛ ሰው" ማለት ነው። አንድ ሰው ሙስሊም ለመሆን " ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም። መሀመድ ደግሞ የእርሱ መልእክተኛ ነው።" የሚለውን የእምነት መግለጫ ከልብ መቀበል እንዲሁም ከታች የተዘረዘሩትን አምስቱን የእስልምና ምሶሶዎች መጠበቅ አለባቸው።

1. የእምነት መግለጫውን ማንበብ
2. በቀን አምስት ጊዜ መፀለይ/ መስገድ
3. የረመዳን ወር ላይ መጾም ( በጾሙ ጊዜ ምንም አይነት ምግብ እና ፈሳሽ መውሰድ አይቻልም። መብላት የሚፈቀደውም ፀሀይ ከጠለቀች በኋላ ብቻ ነው።)
4. ከገቢያችን መስጠት (ከምናገኘው ገቢ 2.5%ቱን ለመስኪዶች እና ለድሆች ይሰጣል)
5. ቢያንስ በህይወት አንድ ጊዜ ሳውዲ አረቢያ ወደ ሚገኘው መካ መንፈሳዊ ጉዞ ማድረግ (ከአንድ ጊዜ በላይ የተጓዘ ሰው በመንፈሳዊነት ከፍ ያለ ቦታ ይሰጠዋል።

እስልምና የክርስትና እና የአይሁድ እምነት ቅጥያ መሆኑን ይናገራሉ። ነገር ግን የስላሴ ትምህርትን እንዲሁም የክርስቶስን አምላክነት በፍፁም አይቀበሉትም። ቅዱስ ቁርአን " የመፅሀፉን ሰዎች አዳምጡ" (መፅሀፍ ቅዱስን እየገለፀ ነው፥ ብሎ ቢያዝም ሙስሊሞች ግን ክርስትያኖች መፅሀፎቹን እንደበረዙት ያምናሉ።

የምእራባውያን ክርስትያኖች የእስልምና ሀይማኖት መስፋፋትን በደንብ ይገነዘባሉ። የእስልምና ሀይማኖት በአለማችን በከፍተኛ ፍጥነት (በአመት በ2.9% እድገት) እያደገ ያለ ሀይማኖት ነው። በአንፃሩ የክርስትና ሀይማኖት በ2.3% እድገት ያሳያል። ክርስትናን ከፋፍለን ስናይ ወንጌላውያን በ5.4% እንዲሁም ጴንጤቆስጣውያን በ8.1% በከፍተኛ እድገት ላይ ናቸው።

ለእስልምና ሀይማኖት እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ያለው ከፍተኛ የሆነ የውልደት መጠን እንደሆነ ይታመናል። ነገር ግን ፀሀፊው ዴብ ኮንክሊን "ሙስሊሞች ለመስፋፋቱ እንደ ምክንያት የሚጠቅሱት ብዙዎች እምነቱን እየተቀበሉት በመሆኑ ነው" በማለት ይናገራል። ለዚህም ምክንያቶቹ

1. እስልምና ሀይማኖት ውስብስብ አይደለም። አንድ ሰው እስልምናን ለመቀበል የሃይማኖት መግለጫውን አምኖ መቀበል፤ ስድስቱን ዋና ዋና አስተምህሮዎችን ማለትም በአንድ አምላክ ማመን፤ በመላእክት፣ በቅዱሳን መፅሀፍት( ከሁለቱም ኪዳናት ከፊሉን እና ቅዱስ ቁርአንን) ፤ በነብያት (ከእነርሱ መካከል እየሱስ እና መሀመድ ይገኙበታል)፤ በፍርድ ቀን እና በቅድመ ውሳኔ ማመን ይጠበቅበታል። ከዚህ በተጨማሪ አምስቱ የእምነት አዕማዶች (ምሶሶዎች) የሚታዩ እና ለመማርም ቀላል ናቸው።

2.. እስልምና የሚለመድ (ለመልመድ ከባድ ያልሆነ) ሀይማኖት ነው። በመቶዎች ከሚቆጠሩ ባህሎች ጋር በሚጣጣም መልኩ ተዋህዷል። በእስልምና ውስጥ የመናፍስት ዓለም አለ የሚለውን የምቃረን አስተምህሮ ያለመኖሩ ያመጣቸውን የጎሳ ህዝቦች በውስጡ ለመቀላቀል አልተቸገረም። እንደ እውነታውም ዛሬም ቢሆን በአለም ከፍተኛ ቁጥር ያለው የእስልምና ተከታይ የተለያዩ የመናፍስት አሰራሮችን ተቀብሎ ይኖራል።

3. እስልምና በባህሪው ከፍተኛ ቅንአት የተሞላበት ሀይማኖት ነው ። የሙስሊሞች አላማ እስልምናን (በምእራቡ አለም) ማስፋፋት ነው። ይህ ደግሞ ሊሆን አይችልም ማለት አንችልም። ጳውሎስ የሰበከባቸው አንዳንድ ቦታዎች አሁን ላይ እስልምና በጣም የተስፋፋባቸው ቦታዎች
ሆነዋል። ኢስታንቡልን እና አሌክሳንድሪያን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል።

በአለም ላይ ከአምስት ሰዎች ውስጥ አንዱ ሙስሊም ነው። በወንጌል ካልተደረሱ የማህበርሰብ ክፍሎች ሙስሊሞች 35% ይይዛሉ። በውስጣቸው ካለው ቅንአት እና የነዳጅ ዶላር በመታገዝ የትም ቦታ የተፈለገውን ያክል ዋጋ ከፍለው እስልምናን ከማስፋፋት ወደኋላ አይሉም። በምእራባውያን ሚስዮናዊያንን ለማሰማራት ከወጣው ወጪ ይልቅ በሰሜን አፍሪካ ያሉ የሙስሊም ሀገራት መንግስታት እስልምናን ለማስፋፋት ያወጡት ወጪ ይበልጣል። ክርስትያኖች በብዛት በሚገኙባቸው ሀገራት ዋና አላማው ክርስትናን ማጥፋት ነው።

ትርጉም ፡- ቤዛዊት በቀለ
ምንጭ ፡- Wikipedia.com
Joshua.org



የዓለማችን ያልተደረሱ የሐይማኖት ክፍሎች
ሒንዱይዝም
አጠቃላይ የእምነቱ ተከታዮች
- 1, 157,913,000 -
አለም አቀፍ የህዝብ ብዛት
በ% ሲሰላ
- 15.2 % -
የሚገኝበት የህዝብ ክፍሎች
ብዛት
- 2,597 -
ያልተደረሱት የህዝብ
ክፍሎች
- 2,375 (91.5%) -

# የሒንዱ እምነት

ሂንዱይዝም የሀሳቦች፣ የልምምዶች እና የእምነቶች ውህድ ስለሆነ ለማብራራት ሊከብድ ይችል ይሆናል። በዚህም የተነሳ ምዕራባውያን እምነቱን ለመረዳት ይቸገራሉ። ሂንዱይዝም በሚጠይቃቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች እና በሚሰጣቸው ምላሾች ከክርስትና ሀይማኖት በጣም የተለየ ያደርገዋል።

1. ሂንዱይዝም እንደ ፍልስፍና፡- በሁሉም ሰው ውስጥ የመለኮት ብልጭታ (Spark of Divinity) አለ። ስለዚህም ሰውን ሀጥያተኛ ማለት እንደስድብ (Blasphemous) ይቆጠራል። ስለዚህም የሰው ክጅ አዳኝ አያስፈልገውም። ቪቭካንዳ እንደሚለውም "ሰውን

ሀጢያተኛ ማለት ሀጥያት ነው"። ጥሩ እና መጥፎ የሚባሉ ነገሮች እንደሌሉ እና የውሸት እይታዎች (illusions) እንደሆኑ፣ ይህ የውሸት እይታም የሚወገደው በእውቀት እንደሆነ ይታመናል። "ድነት" የሚገኘውም ከዚህ አለማወቅ በመላቀቅ እንጂ መፅሀፍ ቅዱስ እንደሚለው ከሀጥያት ነፃ ስንወጣ አይደለም። በሂንዱይዝም "ሀጥያት" የሚባለው ሀዘንን የሚፈጥር ነገር ነው። አንድ ሰው ከሞተ በኋላ እንደገና በሌላ ህይወት እንደገና ይወለዳሉ። እንስሳ ወይንም አትክልaት ሆነው ሊወለዱ ይቻላሉ። ካርማ የጥሩ ስራ ድምር ነው። እነዚህ ስራዎች Ceremonial ወይንም ስነ ስርአቶች ናቸው። እነዚህ መልካም ስራዎች ተጠራቅመው በቀጣይ ህይወት የተሻለ፤ መጥፎ ስራን የሰሩት ደግሞ ዝቅ ያለ ህይወት ይጠብቃቸዋል ተብሎ ይታመናል።

2. በሂንዱይዝም ሰዎች የፈለጉትን አምላክ ካሉት 330 ሚሊየን አማልክት ውስጥ መርጠው ማምለክ ይችላሉ። ድነት የሚገኝባቸው መንገዶችም

1.1 የእውቀት መንገድ በመፈለግ

1.2 በጥሞና እና ጸሎት

1.3 መልካም መንገድ እና ስራ በመከተል ናቸው። ይህ ድነትም ነፍስን ከዳግም ውልደት ዙረት አውጥቶ ከዋናው ምንጭ ጋር እንድትገናኝ ያደርጋታል። (ልክ አንድ የውሃ ጠብታ ወደ ውቅያኖስ እንደሚቀላቀል)።

3. እንደ ታዋቂ እምነት፤ የእምነቱ
ተከታዮች ሒንዱይዝም የሀይማኖቱ የቅድመ አያቶች ባህል፣ የእንስሳ አምልኮ ፣ የቤተ መቅደስ አምልኮዎች፣ አስማት፣ አጋንንትን የማስወጣት ልምምድ፣ አስትሮሎጂ እና የእምነቱ አስተማሪዎች( ጉሩ) አስተምህሮዎች ጥርቅም እንደሆነ ተከታዮቹ ይናገራሉ። ከሀይማኖቱ ዋና ዋና እምነቶቹም ውስጥ አለም ጊዜ በጨመረ ጊዜ እየከፋች እንደምትሄድ፤ የሚዳሰሰው አለም የውሸት እይታ(Illusion) እንደሆነ፤ የቀደሙት ጊዜያት ከአሁን የተሻሉ እንደነበሩ፤ ላሞችን አማልክት እንደሆኑ፤ በሰው ጥረት የሚቀየር ምንም ጉዳይ እንደሌለ ያምናሉ።

ምዕራባዊያን የሒንዱ እምነት ፍልስፍናዎች በአዲሱ ዘመን ስርዓት አስተምህሮ፣ የማሄሽ ዮጊ ጥሞና ልምምድ (Meditation practices of Mahesh Yogi) እና የገንዘብ ድጋፍ በሚጠይቁ የተለወጡ የሃሬ ክሪሽና ተከታዮች በኩል እየተመለከቱ ናቸው። ይህ ግን በአብዛኛው አሉታዊ የሆነ እይታ እንዲኖራቸው አድርጓል። ነገር ግን አብዛኞቹ ሂንዱዎች እውነተኛውን ወንጌል አልሰሙም። ስለክርስትና የሚያውቁት ከክርስትያኖች ህይወት ያዩትን ብቻ ነው።

በኤዥያ ከሚኖሩ 3 ቢሊየን ሰዎች ውስጥ 24% የሚሆኑት ሂንዱዎች ናቸው። አብዛኞቹም በህንድ፣ ኔፓል፣ ባሊ (ኢንዶኔዥያ)፣ በብዙ ቁጥር ቡታን ውስጥ፣ ፊጂ፣ ማውሪሺየስ እንዲሁም በደቡብ አሜሪካ ውስጥ በሱሪኔም እና ጉያና ይገኛሉ።

ለሂንዱዎች እግዚአብሔር የግል የሚባ አምላክ አይደለም፡ "ይንቀሳቀሳልም፣ አይንቀሳቀስም፤ ሩቅም ነው፣ ቅርብም ነው በማለት ብራህማ የሚባለውን መለኮታዊ ሀይል ይገልፁታል። ፍፁም የሆነ አምላክ የሰው ልጆችን አይጠላምም፣ አይወድምም ፤ አያግዛቸውምም፣ አያስተጓጉላቸውም።

ፈጣሪ የሚመለከውም ቅድመ አያቶቻቸው ባመለኩበት መንገድ እና መልክ መሆን አለበት። ዛፍ፣ እንስሳት፣ ምስሎች፣ ሰዎች እና ሌሎች በሚሊየን የሚቆጠሩ አማልክት ሊሆኑ ይችላሉ። ከእነዚህ ውስጥ ጎልተው የሚታዩት ቪሽኑ እና ሺቫ ተብለው የሚጠሩት ናቸው። ቪሽኑ "የአለም ጠባቂ" ሲሆን፤ የሚመለከውም በትስብእቱ(Incarnation) በራማ/ክሪሽና ነው። ሺቫ ደግሞ "አጥፊው" ተብሎ ይጠራል። ብዙ ሂንዱዎች በእየሱስ ክርስቶስ ለማመን ካሰቡ የቤተሰብ አምላክ የሆነውን የኩላ ዴቫታን ቁጣ ሊቀሰቅስ ይችላል በሚል በፍርሃት ይኖራሉ።

በአጠቃላይ የሂንዱይዝም ሀይማኖት በተስፋ መቁረጥ እና ማጣት ውስጥ ይከታል። ምክንያቱም አንድን አምላክ አስቆጥተው ይሁን አይሁን፤ ወደ ድነት እየቀረቡ ይሁን እየራቁ በግልፅ አያውቁትም። ቅድስና እና ብልፅግና አብረው አይሄዱም የሚለው እምነታቸው ደግሞ በቀላሉ ለድህነት እንዲጋለጡ አድርጓቸዋል። እንዲሁም ነፍስ ያለው ነገር ሁሉ ቅዱስ እንደሆነ ስለሚታመን (የሰው ልጆችም ከሞቱ በኋላ ወደ እንስሳነት ይቀየራሉ) ለድህነት ተጋላጭ እንዲሆኑ ሌላኛው ምክንያት ነው። ለምሳሌ በህንድ ውስጥ የአመቱ 30% የእህል ሰብል በአይጦች ምክንያት ይወድማል። በተመሳሳይ በየሜዳው እየተቅበዘበዙ የሚታዩት "የተቀደሱ" ላሞች ለምግብነት ቢጠቀሟቸው ለአምስት አመታት ሀገሪቱን በሙሉ መመገብ ይችላሉ።

ሂንዱይዝም በስርዓተ አውዱ እንደ የማህበራዊ መጠበቂያና እና ዋስትና ነው ነው። ስለዚህም ሂንዱዎች ክርስትናን ቢቀበሉ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ከበሬታ፣ ስራ እና ሀብታቸውን ሊያጡ ይችላሉ። ክርስትናን የተቀበሉ ተማሪ መንግስት ለሂንዱዎች ከሚደረግላቸው የገንዘብ ድጋፍ ውጪ ይደረጋሉ። በአጠቃላይ ክርስትናን መቀበል ከማህበረሰብ ጋር መቆራረጥን፤ የቤተሰብ ስም መጥፋት፣ ለትዳር አለመፈለግ፣ ባስ ሲልም አካላዊ ጥቃት እና ስደት ሊደርስባቸው ይችላል። በቅርቡ የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው 20% ሂንዱዎች ከቤተሰባቸው እና ከማህበረሰቡ ጋር መቆራረጥ ባይኖር ኖሮ ክርስቶስን እንደሚከተሉ ተናግረዋል።

ሂንዱዎች የተለያዩ ሃይማኖቶችን ለማወቅ እና ለመስማት ክፍት ናቸው። በሂንዱይዝም ሁሉም መንገድ ወደ አምላክ ይወስዳሉ ተብሎ ይታመናል ስለዚህም ሁሉም ሀይማኖቶች መልካም ናቸው። ቅድመ አያቶቻቸው ባመለኩበት መንገድ እና መልክ ከሆነ ሁሉም የአምልኮ አይነት ልክ ነው የሚል እምነትም ይከተላሉ፤ እናም ብዙ ሂንዱዎች የክርስቶስ አምላክነትን ይቀበላሉ። በዚህም ምክንያት እነርሱን በወንጌል ለመድረስ አስቸጋሪ ነው። በቀላሉ ክርስቶስን ለመቀበል ፍቃዳቸውን ቢሰጡም፤ ይህ ግን ለእነርሱ አንድ ተጨማሪ አምላክ ወደ ህይወታቸው ከመጨመር ውጪ ሌላ ትርጉም ላይሰጡት ይችላሉ።

ትርጉም ፦ ቤዛዊት በቀለ
ምንጭ ፦ Wikipedia.com
Joshua.org

# የአርሲ ኦሮሞ በኢትዮጵያ

የህዝብ ብዛት - 6,309,00
ዋና ቋንቋ፡ - ኦሮሞ ፣ ቦራና-አርሲ-ጉጂ
ትልቁ ኃይማኖት ፡ እስልምና ( 82.00%)
ክርስትና ተከታዮች ከ ህዝቡ በ % ሲሰላ - 10.00%
የወንጌል አማኞች
ከ ህዝቡ በ % ሲሰላ - 3.80%

## መግቢያ / ታሪክ

የተለያዩ የኦሮሞ ህዝብ ቡድኖች በኢትዮጵያ ውስጥ በጣም በብዛት ተበትነው ይገኛሉ። በተጨማሪም በኬንያ ፣ በሶማሊያ እና በግብፅ ይኖራሉ ። እነዚህ ሕዝቦች በግምት ደርዘን የሚሆኑ የጎሳ ስብስቦችን ያቀፉ ናቸው። እነዚህ ሕዝቦች ስለራሳቸው በሚናገሩበት ጊዜ “ኦሮሞ” የሚለውን ስያሜ ብቻ ይመርጣሉ ። ሁሉም ሰዎች ማለት በሚያስችል ሁኔታ በጋራ ግልጽ በሆነ ዘዬ “ኦሮሞ ፣ ቦራና-አርሲ-ጉጂ” የሚባል ቋንቋ ይናገራሉ ። በትውልድ ስርዓታቸው ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም በሃይማኖት ፣ በአኗኗር ዘይቤ እና በፖለቲካ አደረጃጀት በጣም የተለያዩ ናቸው ። በአሥረኛው ክፍለ ዘመን ኦሮሞ ከአፍሪካ ቀንድ ወደ ምዕራብ በኩል በሱማሊያ እንደተገፋ ይታመናል። ከአማራ እና ከትግሬ ጋር በመሆን የኢትዮጵያን መንግስት እና ወታደራዊ አደረጃጀቶችን ተቆጣጠሩ። በ1700 ዎቹ እና በ1800 ዎቹ እነዚህ ህዝቦች በአቢሲኒያ (በኢትዮጵያ) ፖለቲካ ውስጥ ትልቅ ሀይል ሆነዋል። በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን እስልምናን ተለውጠዋል ።

## አኗኗራቸው ምን ይመስላል?

ኦሮሞ የመዋጋት ባህል ያለው አርብቶ አደር ህዝብ ነው ። የአንድን ሰው ደረጃ የሚለኩት ባለው የከብቶች ብዛት ነው ። ብልሃት፤ የወንድነት ባህሪያት ከጀግንነት እና ከጦር ችሎታ ጋር ተፈላጊ ናቸው። ማሽከርከር ፣ ጦር መወርወርና መዋጋትም ዋና ነገር ናቸው። ከጠላቶች ጋር የሚደረግ ጦርነት ኩራት ቢሆንም በቡድኑ ውስጥ ሰላም ይጠበቃል።

በገጠር አካባቢ የሚገኙ ኦሮሞዎች በዋነኛነት የሚተዳደሩት በእንስሳት እርባታ እና በእርሻ ነው ። የተለመደው መኖሪያ “ቱካል” ወይም በሣር ምንጣፎች የተሸፈኑ እና ከግራር ቅርንጫፎች የተሠራ ክብ ቅርጽ ያለው ጎጆ ነው ። የኮን ቅርፅ ያለው ጣሪያ ጭስ እንዲወጣ የሚያስችል ቀዳዳ አለው። መንደሮቹ የተሰሩት ከ10-80 በሚሆኑ ቤተሰቦች ነው ። በዋናነት የሚመገቧቸው ምግቦቸው የሚያካትተው ዱራ (እህልና ጥራጥሬ) ፣ በቆሎ ፣ ባቄላ ፣ ሩዝ፤ ወተት ፣ ሥጋ እና የዱር ፍራፍሬዎችን ነው ። ቡና እና ሻይ ሁለቱም ተወዳጅ መጠጦች ናቸው ። የኦሮሞ ቤተሰብ የሚመራው ሙሉ ለሙሉ የመከበር ስልጣን ባላው አባት ነው ። ወንዶች ብዙውን ጊዜ አንድ ሚስት ብቻ ያላቸው ሲሆን አንድ ሰው ብዙ ልጆች እና የልጅ ልጆች ሲኖሩት ክብሩ የበለጠ ይሆናል ። የኦሮሞ ወንዶች ገና በለጋ ዕድሜያቸው ጦር እንዴት እንደሚጠቀሙ እና እንዴት ጦረኛ እንደሚሆኑ ስልጠና ይወስዳሉ።

ሰው መግደል በተለምዶ የሙሉ ጎልማሳነት እንዲሁም የአንዳንድ ክብረ በዓሎች አካል ነው። በእርግጥ ፣ በተለምዶ ፣ ለማግባት ዝግጁ የሆነ አንድ ሰው ለሙሽሪት የገደለውን አንድ ሰው በከፊል እንዲያቀርብ ይጠበቅበታል ። አሁን ላይ በሰዎች ፋንታ የዱር እንስሳት ጥቅም ላይ ይውላሉ።

አንድ መሠረታዊ የሆነውና ቡድኑ የሚተወቅበት የኦሮሞ እሴት “ቶኩማ” ይባላል። የኦሮሞ ሃይማኖታዊ ፣ ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ኑሮ በዚሁ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው ። ትብብር ለዚህ ሥርዓት በተለይም ለስራ ዝግጅቶች ማዕከላዊ ነገር ነው። ኦሮሞ በቀላሉ የሚቀረብ እና ማህበራዊ እንደሆነ ይነገራል ።

ለእንግዳ ተቀባይነት እና ለለጋስት ትልቅ ቦታ ይሰጣሉ፤ በተለይ ደግሞ ለቅርብ ዘመዶች እና ወዳጆች። አንዳንድ ኦሮሞዎች በስራ ዕድሎች እና በዘመናዊ ትምህርት በመማረክ ወደ ከተሞች ተዛውረዋል ። ሌሎች ደግሞ ወደ ብሔራዊ የፀጥታ ኃይሎች ፣ ወደ ኢንዱስትሪው የሰው ኃይል ወይም ወደ ንግድ ፣ የትራንስፖርት እና የትምህርት መስክ ገብተዋል ።

## እምነታቸው ምንድን ነው?

አብዛኛው ኦሮሞ ሙስሊም ነው ። ሆኖም ግን ፣ ጥቂት ህዝብ ባህላዊውን የሃይማኖት ስዓታቸውን ይከተላሉ ። እነዚህ የጎሳ ሃይማኖት ተከታዮች “ዋቃ” ተብሎ የሚጠራውን አምላክ ያመልካሉ
። የዋደጃ ድግሶች በተለያዩ ዝግጅቶች የተቀናጀ ሲሆን “ለዋቃ” ክብር ተብሎ እንሰሳ ይሰዋል። ዛሬ እነዚህ በዓላት የሙስሊምን ተጽዕኖ ያንፀባርቃሉ ። ብዙ ሰዎች አሁንም ቁሳቁሶች ማለትም እንደ ዛፎች ፣ ምንጮቹ እና ዐለቶች ያሉ ነገሮች መንፈስ እንዳለባቸው ያምናሉ። በተጨማሪም ጂኒ የተባሉት መናፍስት ሰዎችን ይይዛሉ ተብሎም ይታመናል ። የረመዳን ጾም ወቅት (ሙስሊም ቅዱስ ወር) መጾም በአብዛኛዎቹ ጎልማሶች የሚከበር ሲሆን ሌሎችን የሙስሊም ክብረ በዓላትን የማክበሩ ነገር ውስን ነው ።

## ፍላጎቶቻቸው ምንድን ናቸው?

ብዙውን ጊዜ የኦሮሞ መንደሮች መብራት የላቸውም ። የሕክምና እንክብካቤ ደካማ ሲሆን የመድኃኒት ተደራሽነትም ውስን ነው ። የውሃ አቅርቦታቸውን የሚሟሉት ከወንዝ እና ከምንጮች ነው ።

ክርስትናን ከተቀበሉ አገራት አንዷ ኢትዮጵያ ነች ። የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን መተርጎም የተጀመረው ከ1870ዎቹ ቀደም ብሎ ነው። ሆኖም ለማጠናቀቅ 100 ዓመታት ያህል ፈጅተዋል ። አዲስ ኪዳን የተጠናቀቀው በ1979 ሲሆን ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ በ1995 እ.ኤ.አነው ። ሆኖም ይህ ትርጉም በአሁኑ ጊዜ በትምህርት ከሚሰጠው የተለየ ፊደልን ይጠቀማል ።



ዛሬ በኦሮሞዎች መካከል ክርስቲያኖች ሠራተኞች በከፍተኛ ሁኔታ ያስፈልጋሉ ። እድገት የሚቀጥል ከሆነ እና አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት እንዲተከሉ ከተፈለገ መሪዎችን ማሰልጠንና አዲስ ዓማኞችን ደቀመዝሙር ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው ።

<u>የጸሎት ነጥቦች</u>

· የመከሩ ጌታ ኢትዮጵያዊያ ክርስቲያኖችን ለስራ በኦሮሞዎች መካከል እንዲያስነሳ ጸልዩ ።



· በኦሮሞዎች ላይ ትኩረት አድርገው ለሚሰሩ የቤተክርስቲያን ተካዬች መንፈስ ቅዱስ ጥበብና ሞገስ እንዲሰጣቸው ጸልዩ ።

· የኦሮሞ አማኞች ክርስቶስን ለገዛ ወገኖቻቸው እንዲያካፍሉ እግዚአብሔር ድፍረትን እንዲሰጣቸው ጸልዩ።

· ወንጌልን በድፍረት የሚያውጁ መሪዎች ከኦሮሞ ሰዎች መካከል ጌታ እንዲያድን ጸልዩ።

·በአምልኮ እና ምልጃ ምድሩን የሚያናውጡ የፀሎት ቡድኖችን እንዲያነሳ እግዚአብሔርን ጠይቁ ።

· ለስሙ ክብር የምትሆን የኦሮሞ ቤተክርስትያን እንድትገለጥ ጌታን ጠይቁ።

